
# ትንሣኤ

5/9/1971



አዲሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስና የውስጥ መምሪያ ደንብ።

ዋጋው አምሳ ሳንቲም    ቁጥር 20    ፲፱፻፸፩



የአዲስ አበባና የመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ፡
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት።
የቅዱስ ሲኖዶሱ ሊቀ መንበር።

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# አርእስት

ማውጫ — ገጽ


ደብዳቤዎች ................................ ፩
አዲስ ደንብ ለአዲስ ሥራ ................................ ፪
አዲሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ. ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ... ፫
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ ክርስቲያን የአስተዳደር መምሪያ
የውስጥ ደንብ ................................ ፲፩
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና ................................ ፳
ለአንድ መቅደስ ምን ያህል ቄስ? ................................ ፳፩
ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት በሶሻሊስት ሩማንያ ................................ ፳፪
የመጽሐፍ ቅዱስ ዐምድ ................................ ፳፬


## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅርቡ ዘጠኝ ጳጳሳት በጡረታ መልክ ተገልለዋል ፤ እነዚያ ጳጳሳት ዛሬ የት ይኖራሉ? ዲቁናና ቅስናስ ሊሰጡ ይችላሉ?

በረከት ፍሥሐ
ከአዲስ አበባ

● አቶ በረከት ፍሥሐ ከሁሉ በፊት በክርስቶስ ሰላምታችን ይድረስዎ ። በጡረታ የተገለሉት ጳጳሳት አንዳንዶቹ ወደ ነበሩበት ክፍለ ሀገር ተመልሰዋል፤ አንዳንዶቹም በአዲስ አበባ በመንበረ ፓትርያርኩ አካባቢ ይኖራሉ ። ዲቁናና ቅስና ስለመስጠታቸው ወይም አለመስጠታቸው በአዲሱ ሲኖዶስና መመሪያ ደንብ አልተጠቀሰም። በጽጥታ ብቻ ታልፎአል ። ስለዚህ መልሱ አሻሚ ይሆናል ። ለምሳሌ ይሰጣሉ ልንል እንችል ይሆናል ፤ ምክንያቱም አይስጡ አልተባለምና ፤ አይሰጡም ማለትም ይቻላል ፤ ይስጡ አልተባለምና ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

እኔ ዲያቆን ነኝ ፤ ሚስት አግብቼ ልጅ ወልጃለሁ ግን ሚስቴና እኔ ከመጋባታችን በፊት በአንድ ሠፈር ነበርን ስለዚህ ቅድመ ጋብቻ በግብር ተዋወቅን ፤ እርስዋም ፀነሰች ። ወዲያው ሕጋዊ ጋብቻችንን ፈጸምን ። ይህን ጉዳይ ለክፍለ ሀገሩ ሊ/ ጳጳስ ነገርሁ ። ጳጳሱም በክህነት ማገልገል እንደማልችል ነገሩኝ ። ምክንያቱም እሉ ጳጳሱ "ጋብቻህ ሕገ ወጥ ነውና" ። እኔ ግን ቤተ ክርስቲያንን በክህነታዊ መዐርግ ለማገልገል እፈልጋለሁና ቤተ ክርስቲያን ይህን ችግሬን በምን አይነት መንገድ ልታቃልልኝ ትችላለች?

ዲያቆን ገ/ ሥላሴ
ከሲዳሞ ክፍለ ሀገር

● ዲያቆን ገ/ሥላሴ ጳጳሱ የመለሱልህ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት ተመልክተው ይሆናል ። ስለዚህ እኛ ከርሳቸው በላይ የአስተያየት ፍርድ መስጠት የምንችል አይመስለኝም ። ግን አዲሱ ሲኖዶስ ለጉዳይህ መፍትሔ የሚሰጥበት መንገድ ቢኖር እነሆ ጥያቄህን በሙሉ አውጥተነዋል ። ምናልባት ጉዳዩ ከሚመለከተው ክፍል መልስ በሚገኝ ጊዜ በዚሁ መጽሔታችን ለማውጣት ቃል ገብተንልሃል ።

✶ ✶ ✶

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

መንፈሳውያን መዝሙሮችንና መንፈሳውያን መልእክቶችን ለማግኘት እፈልጋለሁ ። እባክዎ የማገኝበትን መንገድ ይጠቁሙኝ ።

ወ/ሮ አስቴር ጽጌ
ሰበታ

● ወይዘሮ አስቴር ከሁሉ በፊት ስለ መንፈሳዊ ንቃትዎ እናመሰግንዎታለን። የጠየቁአቸውን ነገሮች ሁሉ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ጽ/ቤት ማግኘት ይችላሉ በዚሁ መጽሔት ላይ ባለው አድራሻ ቢጽፉልን ይደርሰናል ወይም ወደ አዲስ አበባ ቢመጡ መ/ ቤታችን በብሔራዊ ሸንጎ ፊት ለፊት ይገኛል በበር አፉላይ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ጽ/ቤት" የሚል ጽሑፍ ይታያል ።




www.ethiopianorthodox.org

ርእስ አንቀጽ

# አዲስ ደንብ ለአዲስ ሥራ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ ክርስቲያን ባለፈው ጥር ወር 1971 ዓ.ም. ዓሥራ ሦስት ጳጳሳትን ከሾመች ወዲ
ህ አዲስ መመሪያ አውጥታለች ከዚህ በፊት መመሪያ ደንብ አልነበራትም ማለት አይደለም ። ግን ጊዜውን ተከ
ትላ ለጊዜው ትውልድ በሚስማማ መንገድ ለመሥራት ትችል ዘንድ ሐዲሳን ጳጳሳትን እንደ ሾመች ሁሉ ደንቡንም
በሐዲስ ሥርዐት አውጥታለች ።

አዲሱ ደንብ የመጀመሪያዋ ሐዋርያዊት ቤተ ርክስቲያን ትመራበት የነበረውን ደንብ በመከተል ማንኛውም
የቤተ ክርስቲያን ሥራ ከህነታዊ መዐርግ በአላቸው ሰዎች እንዲካሄድ ያዝዛል ። ይህም በመሆኑ የእውነተኞች የቤ
ተ ክርስቲያንዋ ተከታዮች ደስታ ፍጹም ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታል ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሩሳሌም የተሰበሰበው የቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በዘመኑ የነበረችው ቤተ ርክስቲ
ያን የምትመራበትን ደንብ ካወጣ በኋላ "...... እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል" ይላል አዎ ጥንታዊት ቤተ ክር
ስቲያን ሥራዋን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ትሠራ ነበር ፤ መመሪያ ደንብም በምታወጣበት ጊዜ የመንፈስ
ቅዱስ ኃይልና ፈቃድ ከመሪዎችዋ ጋር እንደ ነበሩ በላይ የጠቀስነው ጥቅስ ያረጋግጣል ። ከዚህም የተነሣ በየጊዜ
ው ያወጣቻቸው ሕጎች ለጊዜው ብቻ ሳይሆኑ ለዛሬዋም ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሆነው ኖረዋል ። ለምሳሌ ፦
ዲድስቅልያ ፤ አብጥሊስ ፤ ግጽውና ሥርዐት በመባል የታወቁት መጻሕፍት የመጀመሪያዋ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲ
ያን መመሪያ ደንቦች እንደነበሩ የሥነ ጽሑፋቸው ይዘት ያስረዳል ። እነዚያም በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተሠሩ ስለ
ነበሩ ከተሠራባቸው በኋላ እንዲናቁና እንዲወድቁ አልተደረጉም ። እንዲያውም ከቅዱሳት መጻሕፍት ገብተው
እንዲቆጠሩ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ይፈቅዳሉ ።

በዚህ አንፃር የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችም የሚሠሩ ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ጋር እንጂ በራሳቸው ፈቃድ
ብቻ አይደለም ። ለምን? በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አድሮ ይሠራ የነበረ መንፈስ ቅዱስ በዛሬዋም ቤተ ክር
ስቲያን መሪዎች አድሮ እንደሚሠራ የማይታበል ተስፋ በክርስቶስ ተሰጥቷልና ። ስለዚህ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጣው
ደንብ ሁሉ የሰዎች ሥራ ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስም ነውና ክርስቲያኖች ስለ ሰዎች ክብር ሳይሆን ስለ መንፈስ ቅዱስ
ክብር ይቀበሉታል በአፈጻጸሙም ሥርዐት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ እንደመፈጸም አድርገው በሥራ ያውሉ
ታል ። ከጥንት ጀምሮ የነበረ ሥርዐተ እምነታቸውን ይዘው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ብንመለከት በሲኖዶስ፣
የወጣ መመሪያ ሕግ ለማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ምንጭ ነው ሲኖዶሱም ለሃይማኖት ውሳኔዎች
ሁሉ መድበል ነው መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የትምህርት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ ይታመናል ። ስለዚህ እነዚህ ሦስት
ነገሮች ጐን ለጐን ይኖራሉ ። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ያለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ሲኖዶስና መመሪያ ደንብ ልት
ኖር አትችልምና ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ይህን ሥርዐት ትቀበላለችና በአዲሱ ሲኖዶስ የወጣ
ውን መመሪያ ደንብ ለአስተዳደርዋ መሠረት ሲኖዶሱን ለእምነትዋ ወሳኝ መጽሐፍ ቅዱስንም ለትምህርትዋ ምን
ጭ አድርጋ ትሠራለች ታሠራለችም የሥራ አፈጻጸምዋም በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድና መሪነት እንደሆነ ታምና
ለች ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፈቃድ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ነውና ።



# አዲሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

## ቅዱስ ሲኖዶስ

የካቲት 12 ቀን 1971 ዓ.ም.

የኢት/ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ርክስቲያን ቅዱስ ሴኖዶስ አባላት ምልዓተ ጉባኤ አድርጎ ለቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ የተረቀቀውን የሲኖዶስ ደንብ የሲኖዶሱ ዐባላት በፊርማቸው አጽድቀዋል ።

<u>የሲኖዶሱ ዐባላት ስም ዝርዝር</u>

1ኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ሊቀ መንበር
2ኛ/ ብፁዕ አቡነ አብርሃም
3ኛ/ " " እንድርያስ
4ኛ/ " " ማቴዎስ
5ኛ/ " " መቃርዮስ
6ኛ/ " " ዜናማርቆስ
7ኛ/ " " በርተሎሜዎስ
8ኛ/ " " ናትናኤል
9ኛ/ " " ዘካርያስ
10ኛ/ " " መርሐክርስቶስ
11ኛ/ " " ኤልሣዕ
12ኛ/ " " ሰላማ
13ኛ/ " " ታዴዎስ
14ኛ/ " " መርቆሬዎስ
15ኛ/ " " ይስሐቅ
16ኛ/ " " ሳሙኤል
17ኛ/ " " ማትያስ
18ኛ/ " " ጎርጎርዮስ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ርክስቲያን ከተመሠረተችበት ከ330 ዓ.ም. ጀምሮ እስካሁን ድረስ የምትተዳደረው ሐዋርያትና ሊቃውንት በወሰኑት ቀኖና መሠረት ነው ። በየጊዜው ጳጳሳቷ ሲኖዶስ እያደረጉ የሐዋርያትን ትምህርት የማያፋልስ እንደዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ ምዕመናንን ለማገልገል የሚመች ሥርዓት ይሠራሉ ። ይህም በሕገ ቤተ ርክስቲያን የተፈቀደ ነው ።

ከዚህም ጋር በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ አለመግባባት ቢፈጠር በፍትሕ መንፈሳዊ መወሰን ያለበት መሆኑን በመገንዘብ በጠቅላላው ቤተ ክርስቲያናችን በአስተዳደር በአገልግሎትና (በመግቦት) ሀብት በኩል በራሷ ሕግና ሥርዓት በመመራትና በመደራጀት እንድትራመድ በማድረግ በሕግጋት ሁሉ ባለቤት በልዑል እግዚአብሔር አጋዥነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ባለው መንፈሳዊ ሥልጣን መሠረት ይህን ሕግ አውጥቷል ።



### ምዕራፍ 1 ፣

### አንቀጽ 1 ፣
### አጭር ርእስ ፣

ይህ ደንብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 1971 ዓ.ም. የቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

ትርጓሜ ፣

ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፣

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማለት ፣ ከአምስቱ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (ግብፅ ፣ ሶርያ ፣ አርመንና ሕንድ) አንድ የምትሆን ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብላ የምታምን የሀገሯን ሀልውና በታሪክ በነፃነት በባህል በሥነ ጽሑፍ ጠብቃ የኖረች የምትኖር የኢትዮጵያ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው ።

ለ ሲኖዶስ ማለት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን የሚደረግ የጳጳሳት ጉባዔ ነው ። ሲኖዶስ በሐዋርያት ጊዜ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ለመሥራት ተጀምሯል ። ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ቤተ ክርስቲያንን ምድራዊና ሰማያዊ ምግብና ለመመገብ ሲኖዶስ እያደረጉ ድንጋጌና ውሳኔ አስተላልፈዋል ። የሐዋ. ሥራ ምዕ. 15. ቁጥር 19-20 ።

ሐ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት ፣ ፓትርያርኩ ፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የሚያደርጉት ዐቢይ ጉባዔ ነው ።

### አንቀጽ 2 ፣

### የቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማ ፣

1. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅና አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ
2. አገልጋዮቿን ካህናትን በሐዋርያዊ ተግባር ለማደራጀትና እንደዚሁም ችሎታቸውንና ኑሯቸውን ለማሻሻል ፣
3. ምእመናንን ለማብዛትና እንደዚሁም በመንፈሳዊ ዕውቀት ታንጸው በምግባር ፣ በሃይማኖት ጸንተው በክርስቲያናዊ ሕይወት ተጠብቀው እንዲኖሩ ለማድረግ ፣
4. የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ለማሻሻልና በማናቸውም ጉዳይ ራሷን ለማስቻል ፣
5. ወጣቶች የአባቶቻቸውን እምነትና ባህል ጠብቀውና አክብረው እንዲኖሩ (ለመኖር እንዲችሉ) ጥረት ማድረግ ፣

ተግባር

የሲኖዶሱ ተግባር በጠቅላላው በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የበላይ ኃላፊ ሆኖ ተቆጣጥሮ ማሠራት ።

ሀ/ የክርስቶስን ወንጌል መንግሥት ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ማስተማርና ማስፋፋት ፣

ለ/ መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶችን ማቋቋምና ማደራጀት ፣

ሐ/ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደርና አገልግሎት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት እያሻሻሉ መሥራት ፣

መ/ ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚፈቅደው መሠረት በሲኖዶስ የተወሰኑትን ሕግጋት ፣ መመሪያዎች ፣ ደንቦች ትእዛዞችና ውሳኔዎች ማስፈጸም ።

### አንቀጽ 3 ፣
### የቅዱስ ሲኖዶስ አባሎች ፣

የኢትዮጵያ ፓትርያርክና ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ህገረ ስብከቶች የተሾሙ ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ አባላት ናቸው።

### አንቀጽ 4 ፣
### የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ፣

የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሳቢ (ሊቀ መንበር) ፓትርያርኩ ነው ። ፓትርያርኩ በረጅም ጊዜ ሕመም ወይም በሀገር ባለመኖሩ ምክንያት ለመገኘት ያልቻለ እንደሆነ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባሎች መካከል ፓትርያርኩ የወከለው ሰብሳቢ ይሆናል ። ነገር ግን ፓትርያርኩ ይህን ለማድረግ በማይችልበት ጊዜ ከሲኖዶሱ አባላት አንዱ በችሎታው በሲኖዶሱ ድምፅ ብልጫ ተመርጦ ሰብሳቢ ይሆናል ።

### አንቀጽ 5 ፣
### የቅዱስ ሲኖዶስ መሰብሰቢያ ጊዜያት ፣

ፍትሐ መንፈሳዊ በአምስተኛው አንቀጽ እንደሚያዘው በዓመት ሁለት ጊዜ በመንበረ ፓትርያርክ ስብሰባ ያደርጋል ። የመጀመሪያው ስብሰባ በጥቅምት 12 ቀን ይሆናል ። የሁለተኛው ስብሰባ ደግሞ ትንሣኤ በዋለ በሃያ አምስተኛው ቀን ይሆናል ። አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም ግን ፓትርያርኩ ከሲኖዶሱ ቀዋሚ አባሎችና ከሲኖዶሱ ጸሐፊ ጋር በመመካከር በሲኖዶሱ ጸሐፊ አማካይነት ለምልዐተ ጉባዔ ጥሪ ያደርጋል ። ምልዐተ ጉባዔ የሚባለው መላው የሲኖዶስ አባሎች የሚገኙበት ጉባዔ ነው ፣ ከአባሎቹ መካከል በቂ መረጃ ያለው እክል ሲያጋጥመው ግን ጉባዔው ሥራውን ይቀጥላል ።

### ምዕራፍ 2 ፣
### አንቀጽ 6 ፣
### ፓትርያርክ ፣

ፓትርያርክ (ሊቀ አበው) ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ማለት ነው ።

### አንቀጽ 7 ምርጫ
ቁጥር 1 ፣

ስለ ፓትርያርኩ አመራረጥ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው ቁጥር ከሲኖዶሱ አባላት የአስመራጭ ኮሚቴ ይሠየማል ።



www.ethiopianorthodox.org

### ቁጥር 2 መራጮች ፤

ሀ/ የሲኖዶሱ አባላት በሙሉ
ለ/ የገዳማት አበምኔቶች ፤ የአድባራት አስተዳዳሪዎች
ሐ/ ከየሀገረ ስብከቱ ከሰበካ ጉባኤያት የተወከሉ የምዕመናን ተጠሪዎች ፤ ከየሀገረ ስብከቱ ከአምስት እስከ ሰባት ሲሆኑ እነዚህም ዕድሜያቸው ከሰላሣ ዓመት ያላነሰ ሆኖ በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ መሆን አለባቸው ።

### ቁጥር 3 ተመራጮች ፤

ለፓትርያርክነት ማዕርግ እጩ ሆነው የሚቀርቡ ጳጳሳት ናቸው ። ይኸውም በሃይማኖትና በቀኖና ከሚመስሉን ጋር አንድ ነው ። ቁጥራቸውም ከሁለት ማነስ ፤ ከሦስት መብለጥ የለበትም ። ዕድሜያቸው ከሃምሳ ያላነሰ ከስድሳ አምስት ያልበለጠ ይሆናል ። ከተመራጮቹ ሁሉም እኩል ድምፅ ቢያገኙ አስመራጭ ኮሚቴው ዕጣ አጣጥሎ ዕጣው የወጣለት ይሾማል ።

### ቁጥር 4 ፤

የምርጫው ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ በሲኖዶሱ ጸድቆ አዲሱም ፓትርያርክ ቃለ መሐላውን ፈጽሞ መንበሩን ይረከባል ።

### አንቀጽ 8 ቁጥር 1 ፤
### የፓትርያርኩ የማዕርግ ስም ፤

ፓትርያርኩ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ "ብፁዕ ወቅዱስ" ይባላል ። ስሙም በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናት በጸሎት ይጠራል ።

### ቁጥር 2 የፓትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር

ፓትርያርኩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ርእስ በመሆኑ መሠረተ ሃይማኖትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃል ፤ ያስጠብቃል ፤ የቅዱስ ሲኖዶሱንም ጉባኤ ሊቀ መንበር ሆኖ ይመራል ።

### ቁጥር 3 ፓትርያርኩ ፤

በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ስብከትና በውጭ አገርም የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የሚሾሙትን ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት መንፈሳዊ ፍትሕ አንቀጽ 5 በሚያዘው መሠረት ከሲኖዶሱ ጋር ቀብቶ ይሾማል ።

### ቁጥር 4 ፤

ሲኖዶሱ ሲስማማበት ለብፁዓን ጳጳሳት የክብር ስም የመስጠት መብት የፓትርያርኩ ነው ።

### ቁጥር 5 ፤

ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የመንግሥት ፈቃድ ማግኘት በሚያስፈልግበት ጊዜ ከሲኖዶሱ ጋር ተመካክሮ የመጻጻፍ መብት አለው ።

### ቁጥር 6 ፤

የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናትና ከመንፈሳውያን ድርጅቶች ጋር ስለምታደርገው ግንኙነት ከሲኖዶሱ ጋር ተወያይቶ ይወስናል ።

### ቁጥር 7 ፤

የፓትርያርኩ መንበር በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ነው

### ቁጥር 8 ፤

የአዲስ አበባ ከተማ የፓትርያርኩ ሀገረ ስብከት ነው ።

### አንቀጽ 9 ፤
### ከማዕርግ መውረድ ፤

ፓትርያርኩ የተዋህዶ ሃይማኖትን ትምህርተ መለኮት የሚያፋልስ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ ማዕርጉን የሚያጐድፍ ሆኖ ሲገኝ በሲኖዶስ ከተጠና በኋላ በሲኖዶሱ ውሳኔ ከማዕርጉ ይወርዳል ።

## ምዕራፍ 3
### ቁጥር 1 ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ

ፓትርያርኩ በሞት ሲለይ ተዋሕዶ ሃይማኖትን ነገረ መለኮትን በማፋለስ ወይም ክብሩን ባለመጠበቅና በመሳሰሉትም ሌሎች ምክንያቶች ከማዕረጉ ሲወርድ ቅዱስ ሲኖዶስ ዕለቱን መርጦ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርክ ይሾማል ፤ ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ በማዕርገ ጵጵስና ቅድሚያ ካላቸው የሲኖዶስ አባላት መካከል ይመረጣል ። ፓትርያርኩ ካረፈ ከአርባ ቀን በኋላ ወዲያውኑ የአዲሱ ፓትርያርክ ምርጫ ይጀመራል ።

### ቁጥር 2 ተግባር

ዐቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ ፤ ፓትርያርክ እስኪሾም ድረስ የነበረውን ጠብቆ ማቆየት እንጂ መሾም መሻር መጨመርና መቀነስ አዲስ ሥርዓትና ደንቦች ማውጣት አይችልም ።

### ቁጥር 3 ፤

በፓትርያርክ ምርጫ ጊዜ የሲኖዶሱ ሊቀ መንበር ሆኖ ምርጫውን ያስፈጽማል ፤ እሱ ግን ከተመራጮቹ አይገባም።

## ምዕራፍ 4

### ቁጥር 1 የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ ፤

ኤጲስ ቆጶስ ማለት የቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊና ጠባቂ ማለት ነው ።



### ቁጥር 2 ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በድንግልና ከመነኮሱ ቆሞሳት መካከል ይሆናል ።

### ቁጥር 3

ለኤጲስቆጶስነት የሚመረጥ ቆሞስ የሚከተሉትን አሟልቶ ሲገኝ ነው ።

ሀ/ በትውልድ ኢትዮጵያዊ
ለ/ በሃይማኖት ተዋህዶ ኦርቶዶክስ
ሐ/ ከምንኩስና በኋላ በገዳም ቢያንስ ለ3 ዓመት ያገለገለ
መ/ በትምህርተ ሃይማኖት ወይም በነገረ መለኮት በቂ ችሎታ ያለውና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ ፤
ሠ/ ሲኖዶሱ በሚያቋቁመው የካህናት ማሠልጠኛ የሚሰጠውን ትምህርት ፈጽሞ በቂ የምሥክር ወረቀት ያለው ፤
ረ/ በግብረ ገብነቱ የተመሰገነ
ሰ/ ሙሉ አካል ያለው ጤንነቱ የተሟላ
ሸ/ ያስተዳደር ልምድና ችሎታ ያለው
ቀ/ ዕድሜው ከአርባ ያላነሰ ከሃምሳ አምስት ያልበለጠ መሆን አለበት ።

### ቁጥር 4 የኤጲስ ቆጶሱ አመራረጥ

በምዕራፍ 2 በአንቀጽ 1 በተጠቀሰው መሠረት ይፈጸማል ።

### ቁጥር 5 የኤጲስ ቆጶሱ የማዕርግ ስም

ኤጲስ ቆጶሱ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ "ብፁዕ" ይባላል ስሙም በጸሎት ጊዜ በሀገረ ስብከቱ ይጠራል ።

### ቁጥር 6 የኤጲስ ቆጶሱ ሥልጣንና ተግባር

በየሀገረ ስብከቱ የተሾመው ጳጳስ ቅዱስ ሲኖዶስ ከወሰነው ትእዛዝ ሳይወጣ በተሰጠው ሀገረ ስብከት ለቅዱስ ሲኖዶስ ተጠሪ ሆኖ ከሐዋርያትና ከአበው ሊቃውንት ሲያያዝ የመጣውን የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ጠብቆ ይሠራል ያሠራልም ። ካህናትንና ምዕመናንን በመንፈሳዊ መሪነቱ ለማስተማርና ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸምና ለማስፈጸም ለማናቸውም አስተዳደር ሙሉ መብት አለው ።

### ቁጥር 8 ግዴታ ፤

ሀ/ ኤጲስ ቆጶሱ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ካልሆነ በቀር ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ከአሥራ አምስት ቀን የበለጠ መቆየት አይችልም ፤
ለ/ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሚደረገው ምልዓተ ጉባዔ የሥራ ፍሬውን ማቅረብ አለበት ፤
ሐ/ ጳጳሱ በገዜ ዕረፍቱ የጳጳስነት ተልዕኮውን ሲፈጽም ከኖረበት ሀገረ ስብከት ውጭ መቀበር አይገባውም ፤
መ/ ያለ በቂ ምክንያት የጳጳስነት ማዕርጉን በፈቃዱ እንዲተው አይፈቀድለትም ።

### አንቀጽ 10 ቁጥር 1

ከማዕርግ መውረድ በምዕራፍ 2 በአንቀጽ 9 በተጻፈው መሠረት ይፈጸማል ።

### ቁጥር 2 ስለ ኤጲስ ቆጶስ ዝውውር

በመንፈሳዊ ፍትሕ አንቀጽ 5 በተወሰነው መሠረት ለከፍተኛ ዕድገት ወይም በሌላ ምክንያት በቅዱስ ሲኖዶስ ተጠንቶ ካልሆነ በቀር ኤጲስ ቆጶሱ ተቀብቶ ከተሾመበት ሀገረ ስብከት አይዛወርም ። ይህ ቀኖና በኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም እኅት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የሚሠራበት ስለሆነ መተላለፉ ቤተ ክርስቲያናችንን ያስነውራል ።

### ቁጥር 3 የሊቀ ጳጳሱ ከተልዕኮ ማረፍ

ጳጳሱ ከጳጳስነት ተልዕኮው የሚያርፈው በሕመምና በዕድሜ ምክንያት ለመሥራት የማይችል ሲሆን ነው ። በሀገረ ስብከቱ ስሙ በጸሎት ጊዜ ይጠራል ።

## ምዕራፍ 5
### አንቀጽ 11 የሲኖዶሱ ጸሐፊ

የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ከሲኖዶሱ አባላት መካከል በሲኖዶሱ ተመርጦ ይሾማል ። የሲኖዶሱ ጽ ቤት ለሲኖዶሱ ተጠሪ ሆኖ በሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ይመራል ።

### ቁጥር 1 ተግባርና ሥልጣን

የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ለሲኖዶሱ የሚቀርበውን ርእሰ ነገር (አጀንዳ) እያዘጋጀ ለሲኖዶሱ ያቀርባል ።

### ቁጥር 2

በሲኖዶሱ ስብሰባ ላይ እየተገኘ የሲኖዶሱን ቃለ ጉባዔ ይይዛል ።

### ቁጥር 3

ከሲኖዶሱ የሚሰጡትን ትእዛዞች ወደጽሕፈት ቤቱ ያስተላልፋል ፤ ይቆጣጠራል ፤

### ቁጥር 4

በየጊዜው የሚተላለፈው የሲኖዶሱ ውሳኔ ከሥራ ላይ ካልዋለ የሲኖዶሱ ጸሐፊ ለሲኖዶሱ ያቀርባል ሲኖዶሱም ተገቢውን ርምጃ ይወስዳል ።



www.ethiopianorthodox.org

ቁጥር 5

ሲኖዶሱን የሚመለከት ማንኛውንም ጉዳይ በሲኖዶስ ሳያስወስን ማስተላለፍ አይችልም ፣ ቢያስተላልፍም ሕጋዊ ሆኖ አይጸናም ።

ቁጥር 6

ልዩ ስብሰባ እንዲደረግ ባስፈለገ ጊዜ የሲኖዶሱ ጸሐፊ ከዘወትር ቀዋሚ አባላት ጋር በመመካከር የሲኖዶሱን አባላት በጽሑፍ ይጠራል ።

ቁጥር 7

በመንበረ ፓትርያርኩ አንድ ጽ/ ቤትና መዝገብ ቤት ይኖረዋል ።

ቁጥር 8

የሲኖዶሱን ማኅተምና ሰነዶችን ተረክቦ በጥብቅ ይይዛል ፤

ቁጥር 9

የሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ምርጫ በየሁለት ዓመቱ ይፈጸማል ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በድጋሚ ለመመረጥ ይችላል ።

ቁጥር 10

የዋና ጸሐፊው ተጠሪነት ለሲኖዶሱ ነው ።

ምዕራፍ 6

አንቀጽ 12

የሲኖዶሱ ምክትል ጸሐፊ

የሲኖዶሱ ምክትል ጸሐፊ መዐርገ ቁምስና ካላቸው መነኮሳት መካከል ችሎታው ተመዝኖ በሲኖዶሱ ይመረጣል ።

ቁጥር 1 ተግባር

ዋና ጸሐፊው ባለበት ረዳት ሆኖ ፣ በሌለበት ዋና ጸሐፊውን ወክሎ ይሠራል ።

ቁጥር 2

ምክትል ጸሐፊው ተጠሪነቱ ለዋናው ጸሐፊ ነው ።

ምዕራፍ 7

የሲኖዶሱ ተጠሪዎች

በፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት መካከል ሦስት ጳጳስት ከሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ጋር በየስድስት ወር ተራ ገብተው የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ይመራሉ ። ለምልዓተ ጉባዔ የሚቀርበውንም ርእሰ ነገር ያዘጋጃሉ ፤ ይህም ሲሆን ተራ ገብተው ሀገረ ስብከታቸውን እየጐበኙ ነው ።

ምዕራፍ 8

አንቀጽ 13

የመንበረ ፓትርያርኩ መምሪያ ዋና ጸሐፊ ፣

በቅዱስ ሲኖዶሱ ተመርጦ አንድ ጳጳስ ዋና ጸሐፊ ሆኖ በፓትርያርኩ ይሾማል ።

ቁጥር 1 ተግባሩ

ተጠሪነቱ ለፓትርያርኩ ሆኖ ቅዱስ ሲኖዶሱ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በየጊዜው የሚወስናቸውን ጉዳዮች ለየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ጽ/ ቤት ያስተላልፋል ፣ ይቆጣጠራል ። ከየሀገረ ስብከቱ የሚቀርቡትንም ጥያቄዎች እንደአስፈላጊነታቸው ይፈጽማል ፣ ያስፈጽማል ።

ቁጥር 2

የዋናው ጽ/ ቤት የልዩ ልዩ ክፍል መምሪያዎችንና በውስጣቸው የሚገኙትን ዘርፎች ይመራል ።

ቁጥር 3

ከቤተ ክርስቲያን አቋም ጋር የሚስማሙ ሥራዎችን በማካሄድና ለቤተ ክርስቲያን ትምህርት የስብከትና የአገልግሎት ዓላማ የገንዘብ ምንጭ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያን ንብረት የሚለማበትን ፣ ጥቅም የሚያስገኝበትን ዘዴ እያጠና ከሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ ለሲኖዶስ ያቀርባል ።

ቁጥር 4

በየዓመቱ በርክበ ካህናት ጉባዔ የዓመቱን የሥራ ፍሬ የወደፊቱንም ዕቅድ የሚያስረዳ መግለጫ ለሲኖዶሱ ያቀርባል ።

ቁጥር 5

የቤተ ክህነትን ጠቅላላ የዓመት ባጀት አዘጋጅቶ በያመቱ ለርክበ ካህናት ምልዓተ ጉባዔ ለሲኖዶሱ አቅርቦ ያስፈቅዳል ።

ቁጥር 6

ማንኛውም ወጭ የሚደረገው በሱ ፊርማ ነው ፤ እሱ በሌለ ጊዜ በሱ አሳሳቢነት በሚወክለው ሰው ይንቀሳቀሳል ።

ቁጥር 7

ከዚህም ሌላ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚወስንለትን ሌላም ተግባር ሁሉ ይፈጽማል ።



አንቀጽ 14

ቁጥር 1

የአስተዳደር መምሪያ

በአስተዳደሩ መምሪያ የሚገኙ ፣

ሀ/ የሊቃውንት ፣ የሥነ ጽሑፍ የድርሰትና የማስታወቂያ ፣
ለ/ የትምህርት ፣ የስብከት የካህናት ማሠልጠኛና የወጣቶች መምሪያ ፣
ሐ/ የሰበካ ጉባዔና የካህናት አስተዳደር መምሪያ ።
መ/ የጥንታውያን ቅርሳቅርሶችና የመጻሕፍት ጥበቃ መምሪያ ፣
ሠ/ የገንዘብና የንብረት ክፍል መምሪያ
ረ/ የገዳማትና የአድባራት መምሪያ
ሰ/ የውጭ ግንኙነትና የልማት መምሪያ
ሸ/ የፍትሕ መንፈሳዊ መምሪያ

አንቀጽ 15 ቁጥር 2

መንበረ ጵጵስና

የሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና መምሪያ

ሊቀ ጳጳሱ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ ቤት ይኖረዋል ፣ ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ ቤት የሥራ ልምድና ችሎታ ያለውን ቆሞስ ወይም ቄስ መርጦ ዋና ጸሐፊ ፣ ሊቀ ካህናት ብሎ ይሾማል ፣ የመምሪያው መጠን እንደአስፈላጊነቱ ለዋናው ጽ/ ቤት በም.8 በአንቀጽ 14 በቁጥር 1 እንደተጻፈው ይፈጸማል ።

ምዕራፍ 9

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መብት

ቤተ ክርስቲያናችን አምላክ የመሠረታት እንደመሆኑ መጠን ከፖለቲካ ነፃ ሆና የራሷን በራሷ ለማስተዳደር መብት አላት ።

ሀ/ ባቋቋመቻቸው ት ቤቶች ሃይማኖቷንና ባህሏን ለማስተማር ፣
ለ/ ንብረቷንና አካባቢዋን ለማስከበር ፣
ሐ/ የሰንበት ትምህርት ቤቶችንና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለማቋቋም ፣
መ/ የእሁድንና የሌሎችንም ዐበይት በዓላት ለማክበር ለማስከበር ፣
ሠ/ ካህናት ፣ ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃነ ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያን ሥራቸውን በሚመለከት ጉዳይ ቢከሰሱ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ ይታይላቸዋል እንጂ ወደሥጋዊ ዳኝነት እንዳይመሩ ለማድረግ ፣
ረ/ ቤተ ክርስቲያናችን ሕጋዊ አካል ያላት እንደመሆኑ መጠን መብቷንና ልዕልናዋን የሚጻፈ... መንግሥት ጸጥታዋን በመጠበቅ ህልውናዋን አውቆ እንዲያከብርላት የመጠየቅ መብት አላት ።

አንቀጽ 16 የቤተ ክርስቲያን ግዴታ

ከላይ እንደገለጥነው ቤተ ክርስቲያናችን አምላክ የመሠረታት እንደመሆኑ መጠን ከመንግሥት ፓርቲ ገለልተኛ ናት ፣ ይህም ሲባል ድንበር ለማፍረስ የሕዝቧን አንድነት ለመለያየትና ኢትዮጵያን ለመከፋፈል የሚነሳውን ማንኛውንም ተገንጣይና የውጭ ጠላት በመቃወም ድርሻዋን ታበረክታለች ፣ ይህም ባለፈው ታሪኳ የታወቀላት ነው ።

ምዕራፍ 10

አንቀጽ 17

ቁጥር 1 ስለ አብያተ ክርስቲያናት አተካከል

በሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ፈቃድ ካልሆነ በቀር ቤተ ክርስቲያን መትከል በቅዱስ ሲኖዶስ የተከለከለ ነው ።

ቁጥር 2

የቤተ ክርስቲያን መሠረት ሲጣልም ሆነ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ሲባረክ በኤጲስ ቆጶሱ ወይም እሱ በሚወክለው በቆሞሱ ካልሆነ በቀር ከቤተ ክርስቲያን አይቆጠርም ።

ምዕራፍ 11

አንቀጽ 18

የየክፍላተ ሀገሩ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ምድብ መንበር

1ኛ/ የፓትርያርኩ መንበር አዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ሆኖ በአዲስ አበባ አካባቢ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የፓትርያርኩ ሰበካ ናቸው ።

| ሀገረ ስብከት | መንበር | ከተማ |
|---|---|---|
| 2ኛ/ የሸዋ ሀገረ ስብከት | » | አዲስ አበባ |
| 3ኛ/ የወሎ ሀገረ ስብከት | | ደሴ |
| 4ኛ/ የትግራይ ሀገረ ስብከት | » | መቀሌ |
| 5ኛ/ የኤርትራ ሀገረ ስብከት | » | አሥመራ |
| 6ኛ/ የጐንደር ሀገረ ስብከት | » | ጐንደር |
| 7ኛ/ የጐጃም ሀገረ ስብከት | » | ደብረ ማርቆስ |
| 8ኛ/ የሐረርጌ ሀገረ ስብከት | » | ሐረር |
| 9ኛ/ የወለጋ ሀገረ ስብከት | » | ነቀምት |
| 10ኛ/ የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት | » | መቱ |
| 11ኛ/ የከፋ ሀገረ ስብከት | » | ጅማ |



www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| 12ኛ/ የሲዳሞ ሀገረ ስብከት | » | አዋሳ |
| 13ኛ/ የአርሲ ሀገረ ስብከት | » | አሰላ |
| 14ኛ/ የጋሞ ጐፋ ሀገረ ስብከት | » | አርባ ምንጭ |
| 15ኛ/ የባሌ ሀገረ ስብከት | » | ጐባ |
| 16ኛ/ የአጋዴን » | » | ጅጅጋ |
| 17ኛ/ የኢየሩሳሌም » | » | ዶርሡልጣን |
| 18ኛ/ የአሜሪካን አብያተ ክርስቲያናት ሀገረ ስብከት | » | ኒው ዮርክ ይሆናል። |

ከዚህም ሌላ እንደሀገሩ ስፋት አስፈላጊ በሆኑ አውራጃዎች የሀገረ ስብከት መንበር ማቋቋም ሲያስፈልግ እንደአስፈላጊነቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመክሮ ይወሰናል ። በየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ዋና ከተማ ውስጥ ከሚገኙት ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ዋና ከተማ ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በአቅራቢያ ያለው መንበረ ጵጵስና ይሆናል ።

## ምዕራፍ 12

### የቤተ ክርስቲያናችን የውጭ ግንኙነት

#### ቁጥር 1

ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ኦሪየንታል ቸርችስ ከግብፅ ፣ ከሶሪያ ፣ ከአርመን ፣ ከሕንድ ጋር የነገረ መለኮትና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ስላለን በመንበራችን ይቀድሳሉ ፣ በመንበራቸው እንቀድሳለን ፣ የቁርባን አንድነት አለን የክህነት ቀኖናችንም አንድ ነው ።

#### ቁጥር 2

ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግን የነገረ መለኮትና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ስለሌለን ግንኙነታችን የክርስቲያን ወንድማማችነት ብቻ ነው ። በቁርባን አንገናኝም የክህነት ቀኖናችንም አንድ አይደለም ።

## ምዕራፍ 13

### የአፈጻጸም ሥነ ሥርዓት

ይህ የሲኖዶስ ደንብ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ፣ ምዕመናንን ለመምራት የወጣ ሕግ ስለሆነ ከሥራ ላይ እንዳይውል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቃወም የማይፈጽምና የማያስፈጽም ቢኖር በመጀመሪያ ምክርና ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል ። የማይመለስ ሆኖ ከተገኘ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታወግዘዋለች ። ካሁን በፊት ለቅዱስ ሲኖዶስ መመሪያ ወጥተው የነበሩ ደንቦች በዚህ ተሻሽለዋል ።

ይህ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል ።

ይህ ደንብ ወደፊት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድና ትእዛዝ ሊሻሻል ይችላል ።



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ/ክርስቲያን የአስተዳደር መምሪያ የውስጥ ደንብ

## ክፍል 1

1. ይህ መምሪያ እንደሌላው መሥሪያ ቤት ሁሉ የጊዜውን የአስተዳደር ፈለግ ተከትሎ ይሠራበታል ።
2. የቢሮ ሠራተኞች ከተላላኪ እስከ ዋናው ጸሐፊ (ኤጲስ ቆጳስ) በቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከዲያቆን እስከ ዋናው አስተዳዳሪ ድረስ እንዲሁም በዘበኝነትም ሆነ በጽዳት በልዩ ልዩ የመንፈሳዊ አገልግሎት ተግባር በደመወዝ የተቀጠሩ ሁሉ በአንድነት ተጠቃለው የቤተ ክህነት ሠራተኞች ይባላሉ ።
3. ሀ/ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የሥራ መመሪያ ክፍሎች ይኖሩታል ።
   ለ/ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትም ይህንኑ የተከተለ የሥራ መመሪያ ክፍሎች ይኖሩታል ።
   ሐ/ የአውራጃና የወረዳ ቤተ ክህነት ሠራተኞች በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት በአንድ አይነት መመሪያ ይተዳደራሉ ።

### 4. የሥልጣንና የሥራ ተግባር

ሀ/ ዋናው ጸሐፊ

የዋናውን መሥሪያ ቤት የመምሪያ ኃላፊዎች መመደብ የሚችለው ከሲኖዶሱ በማስፈቀድ ነው ።

ለ/ በሀገረ ስብከት ደረጃ ሊቀ ካህናቱን ሂሣብ ሹሙንና ሌሎችንም ሠራተኞች የሚሆኑትን በቂ ችሎታ ያላቸውን በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሰብሳቢነት በጉባዔ እየተመከረበት ከተወሰነ በኋላ በሥራ ውሎ ለመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት በጽሑፍ ይገለጣል ።

ሐ/ የመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት ቁጥር ለደረጃ ዕድገት ለዝውውርና ለደመወዝ ጭማሪ ለመሳሰለው ሁሉ ተገቢ የሆኑትን እየመረመረ ሲኖዶሱ ሲፈቅድና ሲስማማበት በሥራ ላይ ይውላል ።

መ/ ለቤተ ክህነት ጠቅላላ የሥራ አቅዋም ሲፈቀድ ይጠቅማል ብሎ የሚያምንበትን መመሪያ አጥንቶ ለቅዱስ ሲኖዶስ እያቀረበ የማስፈጸም መብት አለው ።

### 5. የአስተዳደር ኰሚቴ ተግባርና ሥልጣን

በዋናው ጸሐፊ ወይም እሱ በሌለ ጊዜ እሱ በሚወክለው ሰብሳቢነት ፣

ሀ/ የደረጃ ዕድገት
ለ/ የደመወዝ ጭማሪ
ሐ/ በደረጃ ዕድገትና ጭማሪ በክፍላተ ሀገር የሚሰጠውን ውሳኔ
መ/ የጡረታ ማውጣትና ማቆየት ጉዳዩን እየመረመረ ለቅ/ሲኖዶስ አቅርቦ ሲወሰን በሥራ ላይ ይውላል ።

### 6. የመንፈሳዊ ፍትሕና ሥ/ሥ/ ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

ሀ/ የገንዘብ ጉድለት
ለ/ የሥራ አፈጻጸም ጉድለት
ሐ/ የሥነ ሥርዓት ጉድለት
መ/ በየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት በጉባዔም ሆነ በትእዛዝ በሊቃነ ጳጳሳቱ ሰብሳቢነት የተሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ ማየት የሚቻለው በመንበረ ፓትርያርኩ የተመደበው ንዑስ ሲኖዶስ መርምሮ ወደ ክፍሉ ሲመራው ነው ።
ሠ/ በክርስቲያናዊ ጋብቻ የተጋቡትን ሰዎች ክርክር ይመለከታል ።
ረ/ በማናቸውም ዓይነት ከዋናው መንፈሳዊ ፍትሕ ጉባዔ የሚቀርቡትንና የሚሰጡትን ትእዛዞች ሁሉ በሕግ አይቶ የመወሰን ሥልጣን አለው ።
ሰ/ በጠቅላላው የመንፈሳዊ ፍትሕ ሥነ ሥርዓት ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሚሰጠው ውሳኔ በሥራ ላይ የሚውለው የአስተዳደር ጉዳይ ቢሆን ለዋናው ጸሐፊ ፤ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና የመንፈሳዊ ጉባዔ ሲሆን ደግሞ ለቅ/ሲኖዶስ ቀርቦ ከጸና በኋላ ነው ፡
ቀ/ በሀገረ ስብከቱ ደረጃ ከላይ የተዘረዘሩት አርእስተ ጉዳዮች በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት ይታያሉ ።

### 7. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ኃላፊነትና ተግባር

የአስተዳደሩ ሥራ በተፋጠነ ሁኔታ እንዲመራ ለየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤቶች ከዚህ የሚከተለው ኃላፊነትና ተግባር ተሰጥቶአቸዋል ።

#### የሀገረ ስብከት አስተዳደር ጉባኤ አቋም

ሀ/ ሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢ
ሊቀ ጳጳሱ በሌለ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ሰብሳቢ
የስብከት ክፍል የሰበካ ጉባዔ ኃላፊ አባል
የሀገረ ስብከቱ ሂሣብ ሹም አባል
የሀገረ ስብከቱ የትምህርትና የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ አባል
የአብያተ ክርስቲያናት መርጃ ክፍል ኃላፊ አባል



www.ethiopianorthodox.org

ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች መካከል በየዓመቱ የሚመረጡ ሦስት አባላት ይሆናሉ ።

### 8. የሀገረ ስብከቱ የአስተዳደር ጉባኤ ተግባር

ሀ/ የደረጃ ዕድገት

ለ/ የጡረታ

ሐ/ የሥነ ሥርዓት (ዲስፒሊን) ጉባኤ እየመረመረ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል ።

### የድምፅ አሰጣጥ

ሀ/ ኮሚቴው በሚመረምረው ጉዳይ ላይ ባልተስማማ ጊዜ በድምፅ ብልጫ ይወስናል ።

ለ/ ድምፁ እኩል በሆነ ጊዜ በሰብሳቢው የተደገፈው ወገን ይፀናል ።

### 9. የሠራተኞች አቀጣጠር

ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል በጽሕፈት ቤት ሠራተኛነት በማንኛውም ዓይነት ሥራ የሚቀጠር ሰው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይና ማዕርገ ክህነት ያለው መሆን አለበት ።

ለ/ አንድ ሠራተኛ በሚቀጠርበት ጊዜ በሀገረ ስብከቱ ወይም በአውራጃው የቤተ ክህነት ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወቂያ ካወጣና ተወዳዳሪዎች በግልጽ ተወዳድረው የሚመረጠው ሰው ይቀጠራል ። በምርጫም ጊዜ ለሥራው ተፈላጊ ከሆነው ችሎታ ጋር የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አጣምሮ ለያዘ ሥልጣነ ክህነት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል ።

### 10. ዝውውር

ሀ/ አንድ ሠራተኛ ለአንድ ሥራ ከአለበት ሥራ ይልቅ በሌላ ሥራ ይበልጥ ተስማሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ወይም ያለበትን የሥራ ቦታ አልተስማማኝም በማለት ዝውውር በጠየቀ ጊዜ ኮሚቴው ጉዳዩን መርምሮ ተገቢ መስሎ በታየው መንገድ ይወስናል ።

ለ/ አንድ ሠራተኛ የሥራ ደረጃውንና ደመወዙን ሳይነካ በሀገረ ስብከቱ የማዛወር ሥልጣን የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ነው ። ሠራተኛው በዝውውሩ ባይስማማ በተዛወረበት ቦታ ሥራውን እየሠራ ለመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት በጽሑፍ ማመልከት ይችላል ፤ የመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤትም ውሳኔ ባለበት ይደርሰዋል ።

### 11. የደመወዝ ጭማሪ

ውሳኔው በሥራ ላይ ውሎ ኮሚቴው በሀገረ ስብከቱ ከሚገኙት ሠራተኞች መካከል የደመወዝ ጭማሪ የሚገባቸውን ከወሰነ በኋላ ለመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት ይገልጣል ። የጭማሪው ድልድል በሚጠናበት ጊዜ እያንዳንዱ ሠራተኛ ፤

ሀ/ ያለውን ችሎታ

ለ/ የፈጸመውን የአገልግሎት ዘመን

ሐ/ ያስገኘውን የሥራ ውጤት

መ/ በሥራው ላይ የሚያሳየውን ትጋት በመዘርዘር ያጠናል ያመዛዝናልም ፤ ኮሚቴው የሚያጠናው ሂሣብ በሥራ ላይ የሚውለው ጭማሪው ከክፍሉ ሊቀ ጳጳስ ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ ነው ።

### 12. የደመወዝ ጭማሪ የማስተካከያ ሁኔታ

ሀ/ የቤተ ክህነትን ገንዘብ ወይም ንብረት ያጕደሉ ከፍለው ሳይጨርሱ የደመወዝ ጭማሪ አይሰጣቸውም ።

ለ/ ያልተወሰነ የዲስፒሊን ጉዳይ ያለባቸው የደመወዝ ጭማሪ አይሰጣቸውም ።

### 13. የደረጃ ዕድገት

ሀ/ አንድ በጀት የተፈቀደለት ክፍት ሥራ በተገኘ ጊዜ ወይም አንድ ሠራተኛ ይዞት የነበረ ሥራ በተለቀቀ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ ከሚገኙት የቤተ ክህነት ሠራተኞች መካከል ተስማሚ የሆነውን ይመርጣል ።

ለ/ በምርጫው ጊዜ ለሥራው ይመጥናሉ የሚባሉት ወይም ይገባናል ብለው ያመለከቱት ሠራተኞች ያላቸውን የትምህርት ደረጃና ጠቅላላ ዕውቀት ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጡት አገልግሎት ያስገኙት የሥራ ውጤት በጠባይና በግብራቸው ለሥራው ያላቸው ተስማሚነት አንድ በአንድ ተመርምሮ ለቀረበው ሰው ይፈቀዳል ።

### ሥነ ሥርዓት

አንድ ሠራተኛ የቤተ ክርስቲያንን ሀብት በማጉደል ሁከት ሠርቶ ሥራ ከበደለበት ጊዜ ጀምሮ የቀረበውን ማስረጃና ጥፋት ፈጽሞአል የተባለው ሠራተኛ የሚያቀርባቸውን መከላከያ በማመዛዘን ኮሚቴው ጉዳዩን መርምሮ ተገቢውን ቅጣት ይወስናል ። የቅጣቱም ዓይነት መምከር ፤ ተግሣጽ መስጠት በደመወዝ መቅጣት ጥፋቱ ከባድ ከሆነ ደግሞ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ከሥራ ማስወጣት ሊሆን ይችላል ። አንድ ሠራተኛ ከሥራ እንዲወጣ ወይም ከደረጃ ዝቅ እንዲል በሀገረ ስብከቱ ሲወሰንበት ለመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል ።

### 14. አበል

አንድ ሠራተኛ ከሥራ ወደሥራ ወይም ከቦታ ወደቦታ በሚዘዋወርበት ጊዜ ለለቀቀው ሥራ ወይም ለቀድሞው ቦታ የሚከፈለው አበል አይሰጠውም አበሉ በሥራው ወይም በቦታው ለተተካው ሰው ይከፈላል ።

### 15. ጡረታና የአገልግሎት ዘመን

ሀ/ አንድ ሠራተኛ ዕድሜው 55 ዓመት ሲሞላ ጡረታ ይወጣል ፤ ሆኖም በተለይ ቅኔ ፤ መጻሕፍትና ወይም ዜማ ለሚያስተምሩ ከፍተኞች መንፈሳውያን መምህራን የጤንነታቸው ሁኔታ የሚፈቅድ መሆኑ እየታየ የአገልግሎት ጊዜአቸው ይራዘምላቸዋል ። ጤንነታቸው የተሟላ ከሆነ ግን ከ75 ዓመት ዕድሜ በፊት ጡረታ አይወጡም ።

16. ለ/ የአገልግሎት ጊዜ የሚራዘምላቸው የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ኰሚቴ አጥንቶ ሀሳብ ሲያቀርብላቸው ነው ።

17. ሀ/ ማናቸውም የቤተ ክህነት ሠራተኛ የሆነ አባል በመጀመሪያ ሲቀጠር በሠራተኛው ምርጫ ሳይሆን እንደሌላው መሥሪያ ቤት ሁሉ በመሥሪያ ቤቱ ትእዛዝ እንደአስፈላጊነቱ በየትኛውም ቦታ በረሃም ሆነ ከተማ ሳይመርጥ በተፈለገበት ቦታ ተመድቦ የመሥራት ግዴታ አለበት ።

ለ/ በክፍለ ሀገር ደረጃ ማናቸውም የቤተ ክህነት ሠራተኛ ተጠሪነቱ ለየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ሆኖ አመዳደቡም ባለው የሥራ ዝንባሌ በትምህርትም ችሎታ መሆን ይኖርበታል ።

ሐ/ ለየሀገረ ስብከቱ ከዋናው መሥሪያ ቤት ኮርስ በመከታተልም ሆነ በሌላ የሥራ አቅጣጫ ተመድበው የተላኩ ሁሉ ምድብ ሥራቸውን በመልቀቅ በማይመለከታቸው የሥራ ተግባር ተሰማርተው ስለሚገኙ ይህ ደንብ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚአስቸኩል በተመደቡበት የሥራ መስክ እንዲውሉ ።

መ/ በሐ. ተራ ቁጥር እንደተገለጸው ሁሉ ስብከተ ወንጌል ለማስፋፋት በሚወሰደው እርምጃ በዚህ ተግባር በይበልጥ ሊያገለግሉ የሚችሉት ኮርስ በመከታተል በስብከት ሥራ የተመደቡ ሠራተኞች ስለሆኑ የሥራ ምድባቸውን ለቀው በማይመለከታቸው የሥራ መደብ ላይ የሚገኙ በአስቸኳይ ወደ ስብከተ ወንጌል ሥራቸው እንዲመለሱ እንደዚሁም ችሎታ ሳይኖራቸው በስብከት ሥራ ላይ የተመደቡ ሲገኙ በየሀገረ ስብከቱ የአስተዳደር ኮሚቴ እያጠና ለችሎታው ተስማሚ ወደሆነው ሥራ እንዲዛወሩ ማናቸው የቤተ ክህነት ሠራተኞች ሁሉ እንደሌላው መሥሪያ ቤት ሠራተኛ በአለው ሥራና ደመወዝ አምኖበት ከተቀጠረ የተሠማራበትን የሥራ ግዴታ ማክበር ይኖርበታል ።

ሠ/ በቤተ ክህነት ሥራ ማናቸውም የሥራ ደረጃ የተቀጠረ ሠራተኛ ሁሉ ከሥራው ሌላ የግል ሥራ ደርቦ ለመሥራት አይችልም ።

ረ/ በተሰጠው የሥራ ኃላፊነትም ሆነ ሌላ የሥራ ድርሻ በሕግ ማከናወን ይኖርበታል ። የተሰጠውን የሥራ ድርሻ ወደ ጐን ትቶ ሌላ ልዩ ጥቅም ለማግኘት ሥራውን የወዘፈ ሠራተኛ በተቋቋመው የአስተዳደር ጉባኤ እየተጠና ሥራውን መበደል ሀገርን እንደመበደል የሚያስቆጥር ስለሆነ አፋጣኝ እርምጃ ይወሰድበታል ፤ ጊዜው የመሥሪያና የለውጥ መሸጋገሪያ ዘመን እንደመሆኑ መጠን ማንም ሠራተኛ የተመደበበትን የሥራ ተግባር ማሸነፍ እንጂ መሸነፍ አይኖርበትም ይህም ማለት ፤

1ኛ/ የሥራ ጊዜን በከንቱ ማጥፋት

2ኛ/ በሥራ ጊዜ ጠጥቶ መገኘት

3ኛ/ በተወሰነው የሥራ ሰዓት ሥራን አክብሮ በሥራ ላይ አለመገኘት ፤

4ኛ/ በሥራ ሰዓት ከቢሮ ውጭ በየአደባባዩ መታየትና ሥራ መፍታት ያስቀጣል ።

18. ሀ/ ማናቸውም የቤተ ክህነት ሠራተኛ በግልጽ ተወዳድሮ በመመረጥ ደረጃ ዕድገት ወይም ሽግሽግ በሚገኝበት ጊዜ ለቦታው የተመደበውን በጀት የማግኘት መብት ይኖረዋል ።

ለ/ ለአንድ ዓይነት ሥራ አንድ ዓይነት ደመወዝ ማግኘት አስፈላጊ ስለሆነ ለዚህ ተግባር የሚውል እስኬል (መመዘኛ) መሥሪያ ቤቱ ማዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ሊያምንበት ይገባል ።

### 19. አልዋንስ

ሀ/ አልዋንስ የሚፈቀደው ለሥራው ነው ።

ለ/ የየመምሪያው ኃላፊዎችም ሆነ የየሀገረ ስብከቱ ሥራ ኃላፊዎች በደረጃም ሆነ በሥራ ኃላፊነታቸው መሠረት ተመሳሳይ አልዋንስ ማግኘት ይኖርባቸዋል ።

### 20. የጡረታ መብትና ግዴታ

ሀ/ ማንኛውም የቤተ ክህነት ቋሚ ተቀጣሪ ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን ፈጽሞ ወደ ጡረታ ሲገለል በአገሪቱ ሕግ መሠረት የጡረታ መብቱ የተጠበቀ ነው

### 21. የዓመት ፈቃድ

ሀ/ ማንኛውም የቤተ ክህነት ሠራተኛ እንደሌላው ሠራተኛ ሁሉ የመንግሥት ደንብ በሚያዘው መሠረት የዓመት ፈቃድ ይኖረዋል

ለ/ ሠራተኛው የዓመት ፈቃድ በሚሰጠው ጊዜ ዕረፍት የሚያደርግበት ወር ደመወዙ አብሮ በቅድሚያ ይከፈለዋል ።

ሐ/ ለሠራተኛው የዓመት ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ ሥ





www.ethiopianorthodox.org

ራው እንዳይበደል በሌላ ሠራተኛ ተደርቦ እንዲሠራ ይደረጋል ።

መ/ በሕግ ከተፈቀደው ጊዜ በኋላ ማንኛውም ሠራተኛ ያለፈቃድ ከሥራው ላይ ቢቀር መሥሪያ ቤቱ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ይችላል ።

22. ሀ/ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች አስተዳደር የሚፈጸመው ቅ/ሲኖዶስ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይሆናል ።

## ክፍል ሁለት

### ስለ ስብከተ ወንጌል መስፋፋት

1. በቤተ ክህነት በኩል ያለው አስተዳደር በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራና ተሐድሶ የሚታይበት እንዲሆን ያስፈልጋል ።

2. ሀ/ ለስብከት የሚዘጋጁትን ሰዎች መምረጥና የሙከራ ወይም የማሠልጠኛ ትምህርት መስጠት ፣

ለ/ ሙሉ የማሠልጠኛ ትምህርት መስጠትና ለሥራ ማሠማራት ፣

3. የሚመረጡት ሰዎች ከመነኮሳት ከቀሳውስት ከዲያቆናት በጠቅላላው ሥልጣነ ክህነት ካላቸው መሆን አለበት ፣

ሐ/ የሚሰለጥኑበት የመጀመሪያ ከወረዳ ተመርጠው በየሀገረ ስብከቱ እንዲሰለጥኑ ማድረግ የሁለተኛው ከፍተኛ ማሠልጠኛ ግን መሥሪያ ቤቱ በወሰነው ቦታ ይሆናል ።

መ/ እነዚህ የሚሠለጥኑት ደቀ መዛሙርት በየወረዳው የቤተ ክህነት ኃላፊና የሰበካ ጉባኤ አባሎች አማካይነት ይመረጣሉ ።

4. ከቤተ ክርስቲያን አመራር ጋር ያለው ግንኙነት የስብከት ሥራ ኃላፊነት ከሊቀ ጳጳሱ ጀምሮ ያሉትን የሚመለከት ስለሆነ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የገዳማት መምህራን የአድባራት አለቆች የገጠር መሪጌቶች የሀገረ ስብከት ፣ የአውራጃ የወረዳ የቤተ ክህነት ሥራ መሪዎች ሁሉ ዋናው ሥራቸው የስብከተ ወንጌል ተሳትፎ መሆን አለበት ።

#### 5. የሕዝብና የሰባኪው ግንኙነት

አንድ ሰባኪ የቤተ ክርስቲያንን ነባር ሥርዓት አጠቃሎ መያዝ አለበት ፤ ጾም ከመሻርና ጠጥቶ ከመስከር የቤተ ክርስቲያንን አርአያ ከሚለውጥ ጠባይ ፈጽሞ የተወገደ መሆን አለበት ። ይህም ከሕዝቡም ሆነ ከካህናቱ ጋር በመተባበር ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት የሚረዳው ስለሆነ ነው ።

6. አማንያንን የሚያስተምሩ ሰባኪዎች የቤተ ክርስቲያንን ነባር ሥርዓት እንዲለማመዱ ማድረግ ይኖርባቸዋል ። ከዚህ በቀር በልዩ ልዩ ሚሲዮናውያን የተሰበኩ ባሉበት ሁሉ ሰባክያን በወንጌል ትምህርት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናቸው ቀዳሚነት ያላት መሆኑን እያስረዱ ከቤተ ክርስቲያን የወጡት እንዲመለሱ የራቁት እንዲቀርቡ ቢያደርጉ ከስብከተ ወንጌል ሥራቸው እንደ አንዱ አድርገው ቢመለከቱት ከፍ ያለ ጥቅም ይሰጣል ። ምናልባትም በዚህ ጊዜ ለክርክር የሚያስቸግራቸው ኃይለ ቃል ቢኖር በደብዳቤና በስልክ ከሊቃውንት ጉባኤ በሚደረገው ግንኙነት ቢወያዩበት የበለጠ ውጤት ይሰጣል ።

#### 7. ሰባኪው ሊጠነቀቅባቸው ከሚችሉት ነገሮች አንዳንዶቹ

ሰባኪው የተላከው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነትና ሥርዓት ሥነ ምግባር ለማስተማርና ለማስፋፋት ስለሆነ እነዚህን ነገሮች ነቅፎ ከማስነቀፍ ደፍሮ ከማስደፈር የሚጠነቀቅ መሆን አለበት ።

8. በመንግሥት ፖለቲካ አለመግባት ፣ የማንኛውንም ሰው ስም ከሕግ ውጭ በስብከት ውስጥ በነቀፋ አለማንሳት እነዚህን ነገሮች የሚተላለፍ ወይም ስብከተ ወንጌልን የሚያደናቅፍ ቢያጋጥም ጉዳዩ በሥነ ሥርዓት ጉባኤ እየታየ ቅጣት እንዲወሰንበት ይደረጋል ።

#### 9. ስብከተ ወንጌል በየቋንቋው

ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋት ለማንኛውም ሕዝብ በቋንቋው ትምህርት መስጠት በይበልጥ ጠቃሚ መሆኑ የታመነበት ነው ፣ ስለዚህ በየሀገረ ስብከቱ ለስብከት ሥራ አመዳደብ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር የብሔረሰቡን የቋንቋ ችሎታ ያላቸውን መምረጥ ጠቃሚ የሥራ ውጤት ስለሚሰጥ የቋንቋ ችሎታ ያላቸውን ማስቀደም ይጠቅማል ።

10. የስብከትን ሥራ በመገናኛ ዘዴ ማስፋፋት በአንድ ጊዜ በሰው ቁጥር ሰባክያኑን እንደመላክ ያህል የሚቆጠር ታላቅ ቁም ነገር ነው ፣ ስለዚህም በመገናኛ ዘዴ ስብከትን የማስፋፋት ሥራ ቤተ ክርስቲያን ተቀዳሚ ተግባሯ አድርጋ ልትይዘው ይገባል ።

11. በመገናኛ ዘዴ ስብከት ስለማስተላለፍ የሚመረመሩት ጉዳዮች ፣

ሀ. ስብከትን የሚያስተላልፉ ሰባክያን በትምህርት የበሰሉ በሥራ ልምድ የደረጁ ፣ ከፉና መልካም የለዩ ሊናገሩት የሚገባቸውን የሚያውቁ በድምጽ ሰውን ለመሳብ ጣዕመ ልሣን ያላቸው (የታደላቸው) ይህንም ሥራ በራሳቸው ስም የማይሠሩት የማይናገሩት የማያስተምሩት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ስም የቤተ ክርስቲያን መልዕክት ድምፅ መሆኑን የተረዱ ሊሆኑ ይገባል ።



ማሪያዎች

የድምፅ መቅረጫ እስቱዲዮ

. ለቤተ ክርስቲያን ከማናቸውም የመሰብሰቢያ ቦታ ተያይዞ የሚገኝ በእጅ ተይዞ የሚሄድ የድምፅ ማጉሊያ

3. የድምፅ መቅረጫ ቴፕሪኮርደር እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ለስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ተፈላጊዎች ናቸው ።

#### 12. ስብከት በጋዜጣ

የጋዜጦች ዓላማ ማንኛውም ጋዜጣ ቢቋቋም ዓላማው ሕዝብ ያላወቀውን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው ፣ ይህም ሆኖ ልዩ አቅጣጫ አለው ጋዜጣውም የመንግሥት ቢሆን በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያሉትን ጉዳዮች የሚከታተል ይሆናል ። መንፈሳዊ ቢሆንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን መካከል ያሉትን ጉዳዮች የሚመረምር ወይም የሚገልጽ ይሆናል ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች በልዩ ልዩ መሥመር ማለት በታሪክ በሥነ ጽሑፍ በቋንቋ ፣ በዕለታዊ አስተያየት ወደፊት ያለውን በመመራመር ትምህርት ሊሰጡበት የሚቻልበት ገጽ ሊኖራቸው ይገባል ። በዚህም መሠረት በመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት በየሣምንቱ የሚታተመው ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ስለ ስብከት መስፋፋት በሐዋርያዊ ድርጅት በየወሩ የሚታተመው ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ በስብከት መስፋፋት ብዙ ትምህርት ሊያበረክቱ የሚችሉ ስለሆነ የስብከት ማስፋፊያ ዓምድ ሊኖራቸው ያሻል ፣ ከዚህም በቀር ሁኔታው እየታየ መጻሕፍቶችና ባጭር ባጭር የሚጻፉ ዝርዝር ወይም ብትን መግለጫዎችን በየሀገረ ስብከት ማዳረስ የስብከትን ሥራ ለማስፋፋት ጠቃሚዎች ናቸው ። ከዚህም በቀር ለስብከትና ለትምህርት መሣሪያነት የሚረዱ ከባድ ጥያቄዎችን የሚያብራሩ በሊቃውንት ጉባኤ እየተጠኑና እየተመረመሩ ታትመው ሊቀርቡ ይገባል አስፈላጊ ሲሆን ስለ ውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጉዳይም እየተከታተለ መግለጫ ይሠጣል ፣ ቢቻልም በውጭ ቋንቋ የወር መጻሕፍቶች ቢኖሩ ለውጭ አብያተ ክርስቲያናት ለመላክ ምቹ ነው።

#### 13. ስለ ትምህርት መስፋፋት

የቤተ ክህነት ትምህርት ቤቶች ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ይሰጥባቸዋል ።

14. በጡረታ በተገለሉት መምህራን ምትክ እንዳይቀጠር የተላለፈው ቤተ ክርስቲያንን የሚጐዳ ስለሆነ ትእዛዙ ተነስቶ ለጡረታ የተመደበው አበል ተከፍሎ በትርፉ በምትካቸው ይቀጠራል ።

15. የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለማስተማር ተመድበው ሕፃናትን የሚያስተምሩ መምህራን የሃይማኖት ሕፀፅ ያለባቸው እንዳይሆኑ ያስፈልጋል ፣ በከፍተኛ ደረጃ ለመምህራንና ለሰባክያን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች ስለሚያስፈልጉ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ፣ የቅዱስ ጳውሎስ ት/ቤት የዝዋይ መምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ፣ የአጼ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት መ ት ቤት ፣ በመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት ሥር ሆኖ ለማሠልጠኛ ትምህርት ቤት እንዲመደቡ ማድረግ ፣ የትምህርቱም ሥነ ሥርዓት አመራር በቤተ ክርስቲያኒቱ ነገረ መለኮት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ፣ በየሀገረ ስብከቱ የተቋቋሙ ት ቤቶችም በዚሁ ዓይነት ይሠራባቸዋል ።

16. ወደ ማሠልጠኛው ትምህርት ቤት እንዲገቡና የውጭ አገር ትምህርት እንዲቀስሙ በዚሁ አንጻር በእስኮላርሽፕ ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ የሚያስፈልግ ሲሆን በግል ፍላጐታቸው ብቻ የሚጠይቁትን ሣይሆን ቤተ ክርስቲያን ይጠቅሙኛል የምትላቸውን በመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ጭምር የበሰሉትን እየመረጠች በመንፈሳዊና በተግባረ ዕድም እንዲሰለጥኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ይላካሉ ።

17. መምህራን ልምምድ እያደረጉ ባሉበት ቦታ በስብከት ሥራ እንዲሠሩ የገዳማት አበምኔቶችና የአድባራት አለቆች ለሹመት በሚመረጡበት ጊዜ ከአራቱ ጉባኤያት አንዱን ለሚያውቁ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ፣ ሆኖም ጉባኤ አስፍተው ወንበር ዘርግተው ማስተማር አለባቸው በቆላ ሀገር ለሚኖሩ መምህራንና ሰባክያን እንዳስፈላጊነቱ የሥራ አበል እንዲከፈላቸው ያስፈልጋል ።

18. ለሰባክያን ለዕለተ ሰንበት መምህራን በሰባኪነት ሥራ ለሚሠሩ መምህራን በቆላ ሀገር ለሚኖሩ መምህራንና ሰባክያን እንደአስፈላጊነቱ የሥራ አበል እንዲከፈላቸው ያስፈልጋል ።

19. ከጥንት ጀምሮ የቆየውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ እምነት ለማናጋትና ለማፋለስ የሚሞክሩትን መናፍቃን እየተከታተለ በዐቃቢነት ለቅዱስ ሲኖዶስ እያቀረበ ማስወሰን የስብከትና ማስታወቂያ ክፍል ኃላፊነት ነው ።

## ክፍል ሦስት

1. ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በሚያዝያ ወር 1970 ዓ.ም. ተሻሽሎ በወጣው ቃለ ዓዋዲ መሠረት ይሠራል ።

### ስለ ካህናት ቁጥርና አበል አከፋፈል

2. የካህናቱን ችሎታ መርጦ በቁጥር መወሰንና ለተመረጡት ካህናት ደንበኛ ደመወዝ ቆርጦ ማስተዳደር አስፈላጊ መሆኑን በማመን ከዚህ የሚከተለው ማብራሪያ ተሰጥቷል የመንፈሳዊ ትምህርት በቂ ችሎታ ኖሮአቸው ቤተ ክርስቲ



www.ethiopianorthodox.org

ያንን በማኅሌት በመምራት ፣ በመቃኘት በማጥመቅ በመቀደስ በማንበብ ፣ በመተርጐም ከሚያገለግሉ ካህናት ይልቅ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ትምህርት ሳይኖራቸው በስም ካህናት ነን እያሉ ልዩ ልዩ ዓለማዊ ሥራ ላይ ተሰማርተው ራሳቸውን በመርዳት ፈንታ ቤተ ክርስቲያንን ተጠግተው በመንፈሳዊ ትምህርት የደከሙት ካህናት በአገልግሎታቸው ያገኙትን ጥቅም እየተካፈሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዳከም ዋና ምክንያት ሆነው ስለሚገኙ በቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉትን ካህናት ቁጥር መወሰን አስፈላጊ ነው ። ከዚህም ጋር እንደአስፈላጊነታቸው ከበዙበት ወደአነሱበት እየተዛወሩ ይሠራሉ ፤ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነታቸው ይወሰናል ።

3. ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት የሚሾሙ ካህናት

በአሁኑ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪነት መሾም የሚገባቸው ከአራቱ ጉባኤ በአንዱ የተመረቁ በትምህርታቸው በግብረገብነታቸው የተመረጡ ምዕመናንንና ቤተ ክርስቲያንን ለማቀራረብ ችሎታ ያላቸው ለምዕመናን በቂ ትምህርት መስጠት የሚችሉ መሆን ስለአለባቸው ለዚህ ይጠቅማሉ የሚባሉት እየተመረጡ እንዲሾሙ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት ገዳማትና አድባራት የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ተመርጠው የሚሾሙ በቅዱስ ፓትርያርኩና በየሀገረ ስብከቱ ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳት ነው ።

4. የዲቁና ፣ የቅስና ማዕረገ ክህነት አሰጣጥ

የቅስናና ዲቁና ሥልጣን ለመቀበል ከሚቀርቡት አንዳዶቹ ለዚህ ማዕረግ ብቁ የሚያደርጋቸውን ትምህርት ሳይማሩ እስካሁን ድረስ በብዛት ሲሰጥ መቆየቱ የታወቀ ነው ። ይህም በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያን የሰጡት ጥቅም የሚጠበቀውን ያህል ባለመሆኑ ወደፊት የዲቆና የቅስና ሥልጣነ ክህነት የሚቀበሉ እንደ ማዕረጉ ሁኔታ የሚገባውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በቅድሚያ መማርና በትምህርታቸውና በችሎታቸው እየተመረጡ ክህነት እንዲቀበሉ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ይህም በየሰበካው ጉባኤ አማካይነት እየተመረጡና ምሥጢረ ሃይማኖት ማወቃቸው በአስተዳደሩ እየተረጋገጠ ሲቀርቡ እንዲፈጸም ሥልጣነ ክህነት የሚቀበሉትም በምንም ዓይነት ገንዘብ እንዳይከፍሉ የተከለከለ ነው ፣ ክህነቱንም ለመቀበል ከወረዳ ወደ ሀገረ ስብከት የሚሄዱትን ድካም ለማቃለል ብፁዐን ጳጳሳት ፕሮግራም እያወጡ በተወሰነ ጊዜ በየአውራጃው እየተዘዋወሩ እንዲሰጡ ።

ለማዕረገ ክህነታቸው ማረጋገጫ የሚሆን የምስክር ወረቀት በየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና ጽ ቤት እየተዘጋጀ የምስክር ወረቀቱን ማሳተሚያ ሂሣብ እየከፈሉ መረጃቸውን መቀበል ይኖርባቸዋል ።



5. የተደራረበ አበል አከፋፈል

በሌላ ሥራ ተመድበው ደመወዝ የሚከፈላቸው በተጨማሪ ከቤተ ክህነት አገልግሎት አበል ስለሚሰጣቸው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ተወስነው በሚገኙት ካህናት ላይ ቅሬታን ፈጥሮ ስለተገኘ በሰበካ ጉባኤ እየተመረመረ ተደራራቢ ቀለብና ሥራ ያላቸው ሁሉ ባንድ ሥራና ደመወዝ ብቻ እንዲያገለግሉ ።

6. በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በቅስና በዲቆና በመዘምርነት በልዩ ልዩ አገልግሎት ታውቀውና ተመዝግበው የሚገኙ ካህናት መታወቂያ ሊኖራቸው አስፈላጊ በመሆኑና ይህም ካህናት የሆኑትንና ያልሆኑትን ለመቆጣጠር ስለሚረዳ በየሰበካው ጉባኤ ኃላፊነት እየተረጋገጠ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፊርማ መታወቂያ እንዲሰጣቸው ፣ በልብስም በኩል እንደየ ማዐረጋቸው የሚታወቁበት ልብስ መልበስ አለባቸው ።

7. አዲስ ስለሚሠሩ አብያተ ክርስቲያናት

ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያና ማደሻ እየተባለ በየቦታው ልዩ ካርኒ በማሳተም በየከተማው እየተዘዋወሩ የገንዘብ እርዳታ የሚጠይቁ እንዳሉ ታውቋል ። ገንዘብም ተቀብለው ለአስፈላጊው ተግባር ሳይውል እየቀረ ብዙ ገንዘብ መባከኑ በየጊዜው ተገልጿል ።

ስለዚህ በሰበካው ጉባኤ ማስረጃ ተሰጥቷቸው በአዲስ አበባ መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ፣ በክፍላተ ሀገር ደግሞ በመንበረ ጵጵስና ጽ/ቤት አማካይነት በአንድ ዓይነት አርማ በታተመ ካርኒ እንዲሠሩ ቢደረግ ፣ የታተሙትን ካርኒዎች ስብዛት ለማወቅና ዝርዝሩንም ለየሀገረ ስብከቱ ለመግለጽ ስለሚቻል በዚሁ መሠረት ይፈጸማል ።

8. በየሰበካው ጉባኤ ስለሚገኙ ካህናት ተግባር

ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት በገጠር በተተከሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት ካህናት ሰፊ አገልግሎት ለማከናወን እንዲችሉ የመኪና መንገድ በማይገባባቸው ወጣ ገባ በሆኑ ከአውራጃና ከወረዳ ከተማ ርቀው ለሚገኙት ምእመናን መንፈሳዊ ትምህርት ለመስጠት ያላሙትንም በማሳመን የሃይማኖት መሠረተ ትምህርት የሚያስተምሩበት በየዓይነቱ ከፊደል ጀምሮ የሚታተሙት መጻሕፍትና ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች እንዲደርሳቸው ይደረጋል ።

9. የሰበካ ጉባኤ ከገበሬ ማኅበራትና ከከተማ የቀበሌ ማኅበራት ጋር ያለው ግንኙነት

ቤተ ክርስቲያንን ለመደገፍ ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት የሰበካ ጉባኤ ከከተማ የቀበሌ ማኅበራትና ከገበሬ ማኅበራት ጋር ግንኙነቱን ማጠንከር አስፈላጊ ነው ። ይኸውም ጉባኤ የከተማ የቀበሌና የገበሬ ማኅበራት እንዲስፋፉ መርዳት ማስተማር ኃላፊነት እንዳለበት ማሳወቅ የከተማ የቀበሌ ማኅበራትና የገበሬ ማኅበራትም ቤተ ክርስቲያንን በመሥራት በማደስ ንዋየ ቅድሳትን በማደራጀት ይህንንና ይህን የመሳሰለውን ሁሉ ለማድረግ ድጋፍ እንዲሰጡ በየቦታው የሚገኙ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት ጥረት ያደርጋሉ ።

10. በቂ ሀብት ስላላቸው አብያተ ክርስቲያናት

አንዳንዶቹ ገዳማትና አድባራት ያላቸው ገቢ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ማስተዳደር ሲችል ብዙዎቹ ደግሞ የሚቀደስበት አልባሳት በማጣት ለዕለት የሚገለገሉበት ጧፍ ዕጣን ፣ ዘቢብ የተቸገሩ መሆናቸው የታወቀ ነው ። በተለይም በገጠር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ይህን የመሳሰለው ችግር ጐልቶ ይታያል ፣ ስለዚህ በዚህ ምክንያት ተቸግረዋል የሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት ዝርዝር ታውቆ ልዩ ልዩ ገቢ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በልብስ ፣ በጧፍና ዕጣን በየዓመቱ በዕርዳታ እንዲደግፉቸው ይደረጋል ።

11. ካህናትን በትምህርት ለማሠልጠን

ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋት የምዕመናንን ፍላጐት ለማሟላት ብዙ ገቢ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በየዓመቱ ለተወሰኑ ካህናት የሚሠለጥኑበት ገንዘብ በየሰበካው ጉባኤ እየተጠና ከገቢያቸው በማውጣት ለካህናት የማሠልጠኛ ኮርስ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና እንዲሁም የቀሳውስትና የዲያቆናት ሚስቶች በየቤተ ክርስቲያናቸው የዕደ ጥበብና ምሥጢረ ሃይማኖት የባልትና ትምህርት የሚገኝበት ዝግጅት ቢደረግ የቤተ ክርስቲያንን አቋም የሚያጠናክር ይሆናል ።

12. ለሰበካ ጉባኤ አባልነት የምርጫ አፈጻጸም

የሰበካ ጉባኤ አባሎች ምርጫ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያዝያ ወር 1970 ዓ.ም. አሻሽሎ ባወጣው ቃለ ዓዋዲ መሠረት ይፈጸማል ።

## ክፍል አራት

## ስለ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተራድኦና ግንኙነት

13. ሀ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት እንደመሆንዋ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራችና በአባልነት የተመዘገበችው በ1940 ዓ.ም. ሲሆን የአባልነት ግዴታዋን ታከብራለች ፣ እንዲሁም ከማኅበሩ ልታገኝ የሚገባትን መብት እንዲጠበቅ ታደርጋለች ።

ለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት እንደመሆንዋ የሀገሪቱ የጥንት ሥልጣኔ አብዛኛውን ጊዜ ከቤተ ክርስቲያንዋ ህልውና ጋር ተያይዞ የቆየ ስለሆነ ታሪካዊነቷንና ጥንታዊነቷን ከነሥርዓቷ አስታውቃለች ።

ሐ ከአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ጽ ቤት በሚወጡት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች መሠረት በጐረቤት አገሮች ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመረዳዳትና በመተባበር ትሠራለች ።

መ በዓለም ላይ የተለያዩ የክርስትና እምነት ተከታዮች መኖራቸው ይታወቃል ። ስለዚህ የዓለም አብያተ ክርስቲያናትን ማኅበር ቻርተር በመጠበቅ ከሁሉም ወገኖች ጋር ግንኙነቷን አጠናክራ እምነቷንና ባሕሏን በመጠበቅ ትምህርቷንና ልማቷን ታስፋፋለች ፣

ሠ የሚወጡት ፕላኖችና የሚታዩት ፕሮጀክቶች በማናቸውም የእርዳታ ሰጭ ድርጅት ተቀባይነት እንዲኖራቸው ተገቢ ዕውቀት ባላቸው ሰዎች የተሠሩና እውነተኛነት ያላቸው የተመሰከረላቸው እንዲሆኑ ታደርጋለች ።

ረ ቤተ ክርስቲያናችን ከውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናትና ድርጅቶች ጋር የምታከናውናቸው ተግባሮችና የምትቀዋላቸው ውሎች በመጽሔት እየተዘጋጁ በዓመት ሁለት ጊዜ እየታተሙ እንዲሠራጩ ማድረግ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከርም ለውጭ አገር ሰዎችና ድርጅቶች ለማሳወቅ ይረዳታል ።

ሰ የልዩ ልዩ ሞያ አሠልጣኞችና የተግባረ እድ አስተማሪዎችን እንዲሁም የአስተዳደር አማካሪዎችንና ኤክስፐርቶችን በእርዳታ ስም ከውጭ ለማግኘት ቤተ ክርስቲያኖችን ትጠይቃለች በዚህ ረገድ የምታገኘውን ርዳታ ታጠናክራለች ።

## ተራድኦ

2. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባል እንደመሆንዋ ለትምህርቷ ማስፋፊያ ፣ ለልማቷ ማደራጃ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊዋ ነው ። በዚህም መሠረት ወደፊትም ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ከዩኒስኮ በየአቅጣጫው እርዳታ የምታገኝበትን ዕቅድ ታዘጋጃለች ።

ሀ ለዚህም በሐምሌ ወር 1970 ዓ.ም. ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት በሲኖዶሱ ተቆጣጣሪነት የሚመራ አንድ ራሱን የቻለ መምሪያ ይኖረዋል ።

ለ/ በመምሪያውም አማካኝነት በገዳማት በአድባራትና በየሀገረ ስብከቱ አብያተ ክርስቲያናት እራሳቸውን በራሳቸው የሚረዱበት የጉጂ እንዱስትሪዎች ይቋቋማሉ ።

3. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

ስም ከውጭ ሀገር በእርዳታ ስም የሚመጣውንና እንዲሁም ለጥንታውያን ቅርሶች መጠገኛ ተብሎ ከዩኔስኮ የሚገኘው ርዳታ ቤተ ክርስቲያኒቱ የታሪክና የቅርስ ባለቤት እንደመሆንዋ ድርሻዋ እየተሰጣት በቅ/ሲኖዶስ ሥር በተቋቋመው መምሪያ አማካይነት በተገቢው ሥራ ላይ ይውላል ። በቅዱስ ሲኖዶስ ሥር ሆኖ የሚሠራው ይህ የውጭ ግንኙነት መምሪያ የእርዳታውን ገንዘብ ወጭ ገቢ እንዲሁም የሥራውን ጠቅላላ ወጪ በዓመት ሁለት ጊዜ ለቅ/ሲኖዶስ ጉባኤ ያቀርባል ።

4. በልማት ላይ ለሚገኙ አገሮች ሁሉ የአምስት ዓመት ፕላን አዋጆችን ማውጣት አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችን የዓመት ፕላኖች በአጥኚዎች እያስጠናች አስፈላጊና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባውንና በየትና በየት ምንና ምን ለሥራ እንደሚያስፈልጋት ተገቢ ጥናት እየተደረገ በየክፍላተ ሀገሩ ተከፋፍሎ ከላይ እንደተገለጸው ለቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ትምህርት ለስብከተ ወንጌል ማስፋፊያ ለካህናት ማሠልጠኛ ለቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳትና ሌላውንም ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ምንጭ ሊያስገኝ በሚችል የተግባረ እድ ቅድሚያ ለቱሪስት መሳቢያ ዝግጅት ማደራጃና ማስፋፊያ ሥራ ይውላል ።

5. በዚህ ደንብ መሠረት በመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤትና በየክፍላተ ሀገሩ የሚሠሩት ሠራተኞች ለሥራ ውጤታቸው ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገበትና ዝርዝር መግለጫ ለኢትዮጵያ ምእመናንና ለውጭ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶችም በመጽሔትና በጋዜጣ በሌላም አስፈላጊ የዚህ ማሠራጫ ሁሉ በየጊዜው እንዲገለጽ ይደረጋል ።

6. ስለ ጥንታዊ የቤተ ክርስቲያን ቅርስ አጠባበቅ

ቤተ ክርስቲያናችን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር የሚያገናኙ ለልማት ተራድኦ ገቢ ከሚያስገኙት አንዱ ጥንታዊ ቅርስና ሥርዓትን መጠበቅና (ማስጠበቅ) ማሳወቅ እንደመሆኑ ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ቅርሳ ቅርስ በስርቆትና በሽያጭ በመሳሰለው እንዳይወሰድ በእሳት ፣ በብል ፣ በዝናምና በዝገት እንዳይበላሹ በየቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ኃላፊነት በሰበካ ጉባኤ ተቆጣጣሪነት ይጠበቃል ።

7. ጥንታውያን ቅርሶች ሲባል መቅደሶችን ፣ መጻሕፍትን ፣ ሌሎችንም ንዋየ ቅድሳትና የመጻሕፍት ትርጓሜዎችን የዜማ ስልቶችን ፣ የግእዝ ቋንቋን ጥንታውያን ሥዕሎችን የሚያጠቃልል ሆኖ ፣

ሀ/ ጥንታውያን መቅደሶች ከመፍረሳቸውና በውስጣቸውም የሚገኙት ሥዕሎች ከመደምሰሳቸው በፊት እንዲታደሱና እንዲጠበቁ ፣ እድሳቱም የጥንታዊ ታሪክነታቸውን መልክና ቅርጽ ምልክቶቻቸውም ጭምር እንዳይለወጡ ጥንቃቄ እንዲደረግበት ።

ለ/ መጻሕፍት ስንል ፣ ብሉያት ሐዲሳት ፣ ሊቃውንት ፣ ድርሳናትና ገድላት የመሳሰሉት በጠቅላላው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ የሚያጠቃልል ስለሆነ መጻሕፍቱ እንዳይደመሰሱ እንዳይበላሹ ተገቢው ጥበቃና ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል ።

ሐ/ የመጻሕፍት ትርጓሜና የዜማ መጻሕፍት የግእዝ ሰዋስዎች በማኅተም እንዲባዙ ተባዝተውም ቢገኙ ያተረጓጐማቸው የቃል ስልት የዜማቸው ላሕይና ይትበሐል ከሊቃውንት ቃል በቃል ካልተሰማ ስለማያረካ የኢትዮጵያ ቅርስ የሆኑ ሊቃውንት ቀስ በቀስ በሞት ከመለየታቸውና ከመቀነሳቸው በፊት ድምጻቸው በየዓይነቱ የድምጽ መቅረጫ ዘመናዊ መሥሪያዎች ተቀርፀው እንዲቀመጡ ፣ ያሉትም መምህራንና ሊቃውንት በክብር ተይዘው እንዲያስተምሩና ተመሳሳይ ደቀ መዛሙርት እንዲተኩ ይደረጋል ።

8. የጥንት ቅርሶች ይጠበቁ ሲባል አዲሶችንም መጨመር አስፈላጊ ስለሆነ እሱም ለተከታይ ትውልድ ወደፊት ቅርስ ሆነው ስለሚተላለፉና ለቤተ ክርስቲያንም መገልገያ ስለሚያሟሉ የገቢ ምንጭም ስለሚሆኑ የቤተ ክርስቲያን ንክ የሆኑ ማንኛዎቹም ዕቃዎች ማለት መጻሕፍት ፣ መስቀል ፣ ጻሕል ጽዋ ፣ ጸናጽል ፣ ከበሮ ፣ አልባሳት ፣ ምንጣፎች እና እንዲሁም ጧፍና ዘቢብ የመሳሰሉት ሁሉ እንዱስትሪነታቸውና ሞኖፖልነታቸው ለቤተ ክርስቲያን ሆኖ ማደራጃው ማከፋፈያውና መሸጫው በቤተ ክህነት ቁጥጥር ውስጥ እንዲሆን በመንግሥት የተደገፈ ሕግ (ድንጋጌ) እንዲወጣ መንግሥትን መጠየቅ ፣

ሀ/ ከማናቸውም ሥራ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው በየገዳማቱ በየአድባራቱና ፣ ገጠር አብያተ ክርስቲያናት ያሉት ንዋየ ቅድሳት በሙሉ በየመልካቸው በቀዋሚ መዝገብ እንዲመዘገቡና ለቁጥጥርም እንዲመች በጥንቃቄ እንዲቀመጡ ።

ለ/ ቤተ ክርስቲያናችንን ለውጭ ዓለማት ለማስተዋወቅና ለማናቸውም ብሔራዊ ትርኢት (ኤግዚብሽን) ወደ ውጭ ለመላክ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመሄዳቸው በፊት ተመዝግበውና ለመመለሳቸው በቂ ዋስትና እንዲያገኙ ተገቢ ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል ።

ሐ/ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ መምሪያ ከፍ ያለ አቅዋም አደራጅቶ ያለፉት ታሪኮች የግእዝ ፊደል ሰዋስው የቅኔ ምርምር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ባህል እንዲዳብር ይደረጋል ።

## ስለ ቱሪስት ገቢ

9. ሀ/ የቤተ ክርስቲያናችንን የውጭ ግንኙነት ከሚያዳብሩት አንዱ የቱሪስት ግንኙነት እንደመሆኑ ቤተ ክርስቲያንና ንዋየ ቅድሳትን የሚጐበኙት ቱሪስቶች የሚገኘው ገቢ ለቤተ ክርስቲያን የገቢ ምንጭ ስለሆነ በየገዳማቱ በየአድባራቱና ገጠር አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት ቅርሶች በሚገባ ተደራጅተው ለጐብኚዎች ምቹ ሆነው እንዲቀመጡና ሕልውናቸው የቱሪስት መሳቢያ ይሆን ዘንድ በመጽሔት በካርድ እየተዘጋጁ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገሮች ይላካሉ ።

ለ/ ጥንታውያኑን ቅርሶች ለመጐብኘት የሚመጡ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን የሚያስጐበኝ ከዋናው የንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ድርጅት መምሪያና በየክፍላተ ሀገር አንዳንድ የቤተ ክህነት ሠራተኞች ከነበጀቱ እንዲመደቡ ሆኖ በዚህ ሥራ የሚመደቡት ሠራተኞችም አሠረ ክህነትና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚያውቁና የቋንቋ ችሎታ ይኖራቸዋል ።

ሐ/ የቤተ ክርስቲያን ቅርሳ ቅርስ ሲጐበኝ ከጐብኚዎቹ የሚገኘው ገቢ ሁሉ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ስም በሚዘጋጀው የገንዘብ መቀበያ ካርኒ እየተሰበሰበ ከየሀገረ ስብከቱ መንበረ ጵጵስና በሚሰጠው መመሪያ ለዚያው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ልማት እንደአስፈላጊነቱ እየተጠና ይመደባል ።

## ሥራ ማስኬጃ

10. ሀ የጽሕፈት ቤት ሥራ ማደራጃ
ለ የሕንፃ አብያተ ክርስቲያናት መርጃ
ሐ የንዋየ ቅድሳት ማደራጃ
መ ለችግረኞች መርጃ የሚሆን ተለይቶ ተደልድሎአል፣ ስለዚህ ከቤተ ክህነት ጠ መሥሪያ ቤት ተፈቅዶ የተላለፈውን ዓመታዊ በጀት ወጭ (በመጠየቅ) በሥራ ላይ ማዋል ።

## የገንዘብ ወጭ ማዘዝና ኃላፊነት

ሀ/ በሀገረ ስብከት ደረጃ ማናቸውም የገንዘብ ወጪ ሊንቀሳቀስ የሚችለው በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት በጉባኤ እየተወሰነ ነው ።

ለ ሆኖም በየጊዜው ለሥራ ማስኬጃ የሚወጣው ሂሣብ የሚከፈለው ሊቀ ጳጳሱና ሊቀ ካህናቱ ተመካክረው ሲስማሙበት ነው ።

ሐ ሊቀ ጳጳሱ በሌለ ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ተወክሎ ሊቀ ጳጳሱ በሚሰጠው መመሪያ የመፈጸም ሥልጣን ይኖረዋል ። የአውራጃዎቹም በዚሁ ደረጃ ከሀገረ ስብከቱ የተላለፈውን ወጪ በመጠበቅ የወጪ አከፋፈሉን ሥራ ይሠራሉ ።

መ በአንዳንድ አውራጃ ሥራ ኃላፊዎች የገንዘብ ያዥነት ሥራ ጭምር በመደረብ ይሠራሉ ስለሚባል ወደፊት የገንዘብ ያዥነት ሥራ ተለይቶ ይሠራል ። ይህም ማለት አዲስ ሠራተኞች በመቅጠር ሳይሆን በበጀት ከሚተዳደሩት ሠራተኞች መካከል እምነት የሚጣልባቸውንና ችሎታ ያላቸውን በመምረጥ የአውራጃ ገንዘብ ያዥ በሌለበት ቦታ በመምረጥ የአውራጃ ገንዘብ ያዥ በሌለበት ቦታ በመደልደል እንዲሠሩ በማድረግ ነው ።

11. የበጀት ዝውውር

በጀት ማዛወር ሲያስፈልግ የተፈቀደውን አርእስትና ሂሣብ በመጠበቅ በደንቡ መሠረት የማዘዋወሪያ ቅጽ ገ በማ 4 መሠረት እያዘጋጁ በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት በጉባኤ የተመከረበት በቀጥታ ከአንድ አርእስት ወደ ሌላ በማዛወር መሥራት ይችላሉ ።

12. በሀገረ ስብከቱ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ስም በሥዕለትና በአትርሱኝ እንደዚሁም ከምዕመናን የሚገኘው ገቢ ገንዘብ በየቤተ ክርስቲያኑ ተቋቁሞ የሚገኘው የሰበካ ጉባኤ በቃለ አዋዲው መሠረት ገቢውን በሚገባ እየተቆጣጠረ ሂሣቡን ለሀገረ ስብከቱ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በየጊዜው ያስታውቃል ።

13. በወጪውም በኩል እንደዚሁ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቀድሞ ሁኔታው ተብራርቶ በሰበካው ጉባኤ አባሎች እየተመከረበት በሊቀ ጳጳሱ ሰብሳቢነት የሚመራው ጉባኤ ሲያጸድቀው ወጪ እየሆነ ይሠራበታል ።

14. ስለ ሂሣብ ማስታወቅ

አውራጃዎቹ ለሀገረ ስብከት መ/ቤቶች የሀገረ ስብከት ጽ/ቤቶች ደግሞ ለመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት ማናቸውንም የገቢና ወጪ ሂሣባቸውን በየዓመቱ መጨረሻ ከሰኔ 30 ቀን በፊት ያስታውቃሉ ።

15. መቆጣጠር

የመንበረ ፓትርያርኩ ጽ/ቤት የየሀገረ ስብከቱን ጠቅላላ የሥራ ይዞታና ሂሣብ ከዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ እየታየ ሠራተኛ በመላክ ይቆጣጠራል ።

ይህ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ጸድቆ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ወደፊት አስፈላጊ ሌላ ማሻሻያ ደንብ ካልወጣ በቀር ጸንቶ ይሠራበታል ። ይህ የሥራ መመሪያ በትክክል በሥራ ላይ ለመዋሉና ለመፈጸሙ የየሀገረ ስብከቱ የሥራ ኃላፊዎች የመቆጣጠርና የማስፈጸም ኃላፊነት አለባቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

## አርባ ካህናት በተግባረ እድ ተመረቁ

ጨንቻ፡- ባለፈው መጋቢት ወር 1971 ዓ.ም. በጋሞ ጎፋ ክፍለ ሀገር በጋሞ አውራጃ በጨንቻ ከተማ በሚገኘው የካህናት ማሠልጠኛ አርባ ደቀ መዛሙርት በቅዱስ መጽሐፍና በተግባረ እድ ትምህርት ሠልጥነው ተመረቁ ። የካህናት ማሠልጠኛው የተቋቋመው በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ርዳታ ሲሆን ኮርሱ የተካሄደው ለ4 ወራት ያህል ነበር የካቶሊካዊት ቤ ክርስቲያን ለዚህ ት ቤት እስካሁን ድረስ 70.000 ብር (ሰባ ሺ. ብር) አውጥታለች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅትም ሦስት መምህራንን በመላክ ለሥራው ተባባሪ ሆኗል ።

## መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሩሲያ ተላከ

ራሺያ፡- ባለፈው የጥር ወር 1971 ዓ.ም. የተባበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በሩሲያ ቋንቋ የታተሙ 25.000 የመጽሐፍ ቅዱስ ኮፒዎችንና 5.000 የመጽሐፍ ቅዱስ ማውጫዎችን ወደ ሞስኮ ልኮአል ። በአንድ ሳምንት ውስጥ ከመቶ ስድሳው እጅ ለአብያተ ክርስቲያናት ታድሏል ። በየካቲት ወር መጀመሪያ ላይ የተላኩት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በክርስቲያኖች እጅ ፈጽመው ገብተዋል ሲል ወርልድ ሪፖርት ገለጠ ቁ. 107 የካቲት 1979 (1971)

## በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ላይ ስደት እንደሌለ ተገለጠ

ጄኔቫ፡- ባለፈው ጥር 1971 ዓ.ም. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መልእክተኞች ኢትዮጵያን ጉብኝተው ከተመለሱ በኋላ በኢትዮጵያ ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲያናት ላይ በሃይማኖት ምክንያት ስደት አለመኖሩን ገለጡ ሲል ኢኩዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ቁ. 6 46ኛ ዓመት መጋቢት 1 ቀን 1979 (1971) አስታወቀ ።

## ዓለም አቀፍ ጥናት ስለ ሴቶች መብት

ጄኔቫ፡- በመጭው ሰኔ ወር 1971 ዓ.ም. ለ6 ቀናት ስለ ሴቶች መብት በጄኔቫ ስብሰባ ይደረጋል ስብሰባው በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ውስጥ በሴቶች ሊቀ መንበር በወይዘሪት ብርጋሊያ ባም ኃላፊነት ይካሄዳል ። ወይዘሪትዋ እንደገለጡት ጉባኤው ከሚወያይባቸው ጉዳዮች መካከል አንዳንዶቹ በላቲን አሜሪካ ስላሉ የፖለቲካ እስረኞች ሴቶች ማንበብና መጻፍ ስለማይችሉ ሴቶች በጨርቃ ጨርቅ እንዱስትሪና በማድ ቤት ስለሚሠሩ ሴቶች ይሆናሉ። በተጨማሪም የጥናቱ ጉባኤ በሦስተኛው ዓለም ውስጥ በማንኛውም የሥራ ጠባይ በሴቶች ላይ ስለሚደረገው የፆታ ልዩነት ሁሉ ለመመልከት ይሞክራል ። ብርጋሊያ ይላሉ "በመልማት ላይ ባሉ አገሮች የሚገኙ ሴቶች አብዛኛዎቹ ደስተኞች አይደሉም" በእርግዝና ወራት ምንም አይነት የሕክምና ርዳታ አይደረግላቸውም ፣ ልክ አይደለም? ሲሉ ወይዘሪት ብርጋሊያ መጠቆማቸውን ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ገለጠ ። ቁ. 8 46ኛ ዓመት መጋቢት 15 ቀን 1979 (1971) ዓ.ም.



# ለአንድ መቅደስ ምን ያህል ቄስ ?

በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምስት ቀሳውስት ወይም አሥራ ሁለትና ከዚያ በላይ የሚሆኑ ልኡካን (ቀሳውስትና ዲያቆናት) ያገልግሉ የሚል መለኮታዊ ትእዛዝ የለም ። አንድ ቄስ ብቻም ያገልግል የሚል ትእዛዝ እንደሌለ ግልጥ ነው ።ሁሉም ሰው ሠራሽ ትእዛዝ እንደሆነ እናውቃለን ። እርግጥ በሰዎች ቢሠራም የሠሩት ሰዎች መንፈሳውያን እንደሆኑ ይታመናል ። ይሁን እንጂ ዛሬም ያሉ ሰዎች አንድ ሥራት ቢሠሩ በመንፈስ ይሠራሉና መንፈሳውያን መሆናቸውን እንቀበላለን ።

በዓለም ሁሉ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን አንድ ቄስና ሁለተኛ ረዳት ዲያቆን ይሾማሉ እነዚህ ሁለት ቀሳውስት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ይፈጽማሉ ከዚያም ሌላ አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አንድ ቄስ ብቻ እንዲያገለግል ሥራት አላቸው ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለ አምስት ካህናት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፈጸሙ ታዝዛለች ካህናቱ ማለት ሁለት ቀሳውስትና ሦስት ዲያቆናት

ካልሞሉ ቅዳሴ አይቀደስም ይህ ሥርዐት ከየት የመጣ ይሆን በስንተኛው ዓመት በስንተኛው ሲኖዶስ በማንኛው ርእሰ ቤ/ ክርስቲያን ተወስኖ ይሆን ? ብሔራዊና ልማዳዊ ሥርዐት ብቻ ነው ከማለት በቀር ከዚያ አገር መጣ ለማለት አንችልም ። ከእኅት (እኅቶች) አብያተ ክርስቲያናት ከእስክንድርያ ከሶርያ ከአርማንያና ከእንድያ የመጣ ሥርዐት ነው እንዳንል እነሆ እነዚያ በአንድ ቄስ ብቻ ሥርዐተ ቅዳሴን ሲፈጽሙ እናያለን ምናልባት ለማየት ወይም ለመጠየቅ የሚፈልግ ቢኖር በላይ ከተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶች በዚሁ በከተማችን ይገኛሉና መጎብኘትና መጠየቅ ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ቤ/ ክርስቲያን በአምስት ቀሳውስት ሥርዐተ ቅዳሴን እንደምትፈጽም ተናገርን እንጂ በአንድ ቤ/ ክርስቲያን ከ50 - 80 የሚደርሱ ካህናት ይገኛሉ ከዚህ ላይ አስተያየቴን ግልጥ ለማድረግ እፈልጋለሁ ችግሩ ካህናት ለምን በዙ ማለቴ አይደለም ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ከአንድ በላይ ካህን በአንድ ቤተ ክርስቲያን እንዲኖር ለምን ሥርዐት ወጣ ? የሚለው ሀሳብ ነው ። የዚህ መልስ ከቅዱስ ሲኖዶስ እንደሚሰጥ ተስፋ አደርጋለሁ ።

ይመረመር ዘንድ የሚገባ ሌላ ነገርም አለ ። ይኸውም በቅዳሴ ማርያም ቁ. 114 - 116 ይህን የሚረዳኝን ካህንና እኔን እንደ ኒቆዲሞስና ዮሴፍ አድርገን፤ ይህን የሚያገለግል ዲያቆንም ወደ ከፍተኛ የክህነት መዓርግ አድርሰው" ይላል ከዚህ ላይ ሦስት አገልጋዮች ብቻ መጠቀሳቸውን እናስተውል በዚህም መሠረት ለአንድ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉ ሦስት ካህናት ብቻ እንደሆኑ መረዳት አያዳግትም ታዲያ አምስት የሚለው ቁጥር ከየት መጣ ? በሥርዐተ ቅዳሴው ላይ በተጠቀሰው ቀኖና ደግሞ ካህኑ አንድ ብቻ መሆኑ ተገልጦአል ዲያቆኑ ግን እንደ ቀዋሚ አገልጋይ ሆኖ አልተጠቀሰም (ሥርዐተ ቅዳሴ ቁ. 63) ስለዚህ ምንጊዜም ቀዳሹ አንድ ካህን እንጂ አምስት አይደሉም ሌሎች ግን ረዳቶች ናቸው ። አንዱ ካህን ትጉሕና ንቁሕ ከሆነ ረዳቶችአያስፈልጉትም ። አሁንስ ለምን ያስፈልጉታል?

ምናልባት በዚህ ላይ አምስት ቢሆኑ ምን ችግር አለ ? ከአምስቱ ቁጥርስ ለምን ይወርዳሉ ? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል አዎ ችግሩ ግልጥ ነው በቤተ ክርስቲያን ያሉ የካህናትን ኑሮ ብንመለከት እጅግ አሰቃቂ ነው ። አንድ ካህን በወር 30 የኢ.ት. ብር ያገኛል ግን ለዚህ ካህን ዐሥር ልጆች ይኖሩታል ራሱና በዓልተ ቤቱ ድምር ዐሥራ ሁለት ቤተ ሰቦች ይሆናሉ እነዚህ ቤተ ሰቦች እያንዳንዳቸው በወር 2.50 የኢ.ት. ብር ያገኛሉ ማለት ነው ። እንግዲህ ይህን ኑሮ ከጊዜው ሁኔታ ጋር በማወዳደር እንመልከት ። እጅግ የሥቃይ ኑሮ ሆኖ እናገኘዋለን ይህ ብቻ አይደለም የካህኑ ልጆች ትምህርት የትምህርት መሣሪያ ልብስና ሌላም ነገር ሁሉ ያስፈልጋቸዋል ይሁን እንጂ ሠላሳው ብር ለዚህ ሁሉ ጣጣ አይበቃም የካህኑ የወር ደመወዝ ሠላሳ ብቻ ሊሆን የቻለ ሌሎች ሠላሳ ካህናት በአንድ ቤተ ክርስቲያን ስላሉና ለእነዚያም ሁሉ ለእያንዳንዳቸው ሠላሳ ብር ስለሚከፈል መሆኑ ግልጥ ነው ። ነገር ግን አንድ ቄስ ለአንድ መቅደስ ቢሆን ኖሮ በቂ ደመወዝ ለማግኘት የተስተካከለ ኑሮ ለመኖር በተቻለ ነበር ።

ያለፈው አልፏል ዛሬም ያሉት ካህናት ይበተኑ የሚል የለም ። ለወደፊቱ ግን ከአሁን ጀምሮ ቢታሰብበት መልካም ይመስለናል ወደፊት ቤተ ክርስቲያን ራስዋን በራስዋ በምትረዳበት ጊዜ ምእመናን የሚያዋጡት ምጽዋት ለ50 ካህናት የሎሚ ሽታ ያህል ነው ለአንድ ካህን ግን በቂ መተዳደሪያ ይሆናል ዛሬም ቢሆን ቅሉ የአንድ መቅደስ ካህናት ቁጥር የሚቀነስበት ምክንያት ይኖራል ይኸውም በገጠረ ኢትዮጵያ አንድ ካህን እንኳ የማይገኝባቸው አብያተ ክርስቲያናት አሉ ። ስለዚህ ለእነዚያ ሁሉ ካህናት እንዲኖራቸው ቢደረግ አንድ ቄስ ለአንድ መቅደስ የተባለው ሕልማዊ ሥርዐት የመንገድ ጥርጊያውን ሊጀምር እንደሚችል እንገምታለን ። ይህን ጽሑፍ ለመደምደም ያህል ፡- አንድ ቄስ ለአንድ መቅደስ ስንል የካህናት የኑሮ ደረጃ እንዲስተካከል ችሎታቸው እንዲጣራ ካህናት የሌሉባቸው አብያተ ክርስቲያናት ካህን እንዲኖራቸው የአንድ ሰበካ ምእመናንም አንድ መንጋ ሆነው አንድ እረኛ እንዲኖራቸው ለመጠቀም እንጂ ዛሬ ያሉ ካህናት እጅግ በዝተዋል ማለታችን አይደለም ። እርግጥ በአዲስ አበባ በአንድ ቤ/ ክርስቲያን ብዙ ትርፍ ካህናት ይገኛሉ ። በገጠሪቱ ቤ/ ክርስቲያን ደግሞ የተዘጋውን በር የሚከፍት ካህን የለም ይህም የሆነው ያ የገጠሩ ካህን ወደ አዲስ አበባ ስለመጣ እንጂ በከተማችን መንፈሳዊ ሴሚናር ኖሮ በዚያ ሠልጥኖ ስለ ተመረቀ እንዳይደለ እናውቃለን ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም ውስጥ እንጂ ከዓለም ውጭ አይደለችም ። ስለዚህ እንደሌሎች የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድ ቄስ ለአንድ መቅደስ እንደሚበቃ ሥርዐት ብታወጣ ምን ይከለክላታል? ሲኖዶሱስ ስለዚህ ምን ይላል?

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

## የማይሠራ ፡ አይብላ ።

፮ወንድሞች ሆይ ፡ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን
ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን ። ፯እኛን ልትመስሉ እን
ዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና ፤ በእናንተ ዘንድ
ያለ ሥርዓት አልሄድንምና ፤ ፰ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ
እንዳንከብድበት ፡ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን
እንኖር ነበር እንጂ ፡ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም።
ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ
ዘንድ ነበር እንጂ ፡ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም ። ፲ደግ
ሞ ከእናንተ ጋር ሳለን ፡- ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን እዘ
ናችሁ ነበርና ። ፲፩ሥራ ከቶ ሳይሠሩ ፡ በሰው ነገር እየገቡ ፡
ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰም
ተናልና ። ፲፪እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እን
ጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዝዛቸ
ዋለን እንመክራቸውማለን ። ፲፫እናንተ ግን ፡ ወንድሞች ሆይ ፡
መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ ።

፲፬በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ ማንም
ቢኖር ፡ ይህን ተመልከቱት ፡ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር አትተ
ባበሩ ። ፲፭ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ ጠላት
አትቍጠሩት ።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ።
☎ 122033 ✉ 30750
አዲስ አበባ

ሮሜ ፲፱፻-፲፫



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org